الدعوة

# ተውሂድን እንዴት እንረዳለን?

ዝግጅት:- ሙሐመድ አህመድ ባሽሚል

# كيف نفهم التوحيد ؟

تأليف
محمد بن أحمد باشميل

أمهر

# ተውሂድን እንዴት እንረዳለን?

ዝግጅት፡- ሙሐመድ አህመድ ባሽሚል

بسم الله الرحمن الرحيم

# የአሳታሚው ማስታወሻ

ከፍተኛ ምስጋና ለአላህ ለአለማት ጌታ ይሁን ሰላትና ሰላም በነብያችን ላይ ይውረድ።

በመቀጠል "ተውሂድን እንዴት እንረዳለን?" በሚል ርዕስ ሼህ ሙሐመድ አህመድ ባሽሚል የተባሉት ደራሲ በአረብኛ ቋንቋ ያዘጋጁትን መጽሐፍ የአማርኛ ትርጉሙን ለአንባብያን ለማቅረብ ስለበቃን ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል።

መጽሐፉ ለኢስላም የጀርባ አጥንት የሆነውን ተውሂድን ይኸውም ማንኛውም የሰው ልጅ ማወቅ የሚገባው መሠረታዊ ትምህርት ሲሆን ፣ በቁርአንና በትክክለኛ ሐዲስ ላይ በመመርኮዝ በጣም ግልፅና ለስለስ ባለ መንገድ በመጽሐፉ አዘጋጅና ሁሌም በአንድ ጉዳይ ብቻ እንጂ በመይለያዩት ባልደረባው መካከል የተከሄደውን የተለያየ አመለካከት ተውሂድን ይረዱ ዘንድ ለአንባብያን ያቀርባል።

እኛ በበኩላችን ትርጉሙን በጥራት ለማዘጋጀት ያልተቆጠበ ጥረት አድርገናል ፣ ነገር ግን ከማንኛውም የሰው ልጅ ሥራ ስህተት ስለማይጠፋ በሚቀጥለው ዕትም እንድንጠቀምበት የተከበራችሁ አንባብያን አስታየታችሁን እንድትለግሱን በአክብሮት እንጠይቃለን።

በተጨማሪም ይህን መጽሐፍ በሀገሪቷ ውስጥ በሚነገሩ ቋንቋዎች ለመተርጎምና ለማሳተም ለረዱን ወገኖች በሙሉ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን።

ኢስላማዊ ደዕዋና ዕውቀት ማኅበር
አዲስ አበባ
23/3/2001

*በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው*

የአለማት ጌታ ለሆነዉ አላህ ምስጋና ይግባዉ ፣ የአላህ ሰላትና ሰላምታ የነቢዮችና የመልዕክተኞች መደምደሚያ በሆኑት ነቢዩ መሐመድ ላይ ይሁን፤

አላህ (ሱ.ወ) ፍጥረታትን ፈጥሮ መልዕክተኞችን የላከዉ እሱን ብቻ እንዲያመልኩት እንጂ ሌላ ለምንም አይደለም አላህ(ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

وَمَاخَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ

"ጂንም ሆነ ሰውን ሊገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኩም"
(አል ዛሪያት)

በጣም አሳዛኙና አስለቃሹ ነገር ብዙሐኑ ያልተማረዉ (ጃህሉ) የሙስሊሙ ህብረተሰብ የአምልኮን ትክክለኛ ትርጉም ባለማወቃቸዉ ከአላህ ሌላ ላሉት ፍጥረታት አምልኮን በማድረግ ከኢስላም በሚያስወጣዉ ትልቁ ሽርክ ዉስጥ ይወድቃሉ።

ይህም የሚሆነዉ በፍርሃትና በመተናነስ ወደ ተቀበሩት ነቢያት፣ ወሊዮችና መልካም ሰዎች (ሷሊሆች) በዱአእ ፣ በመመጀን ፣ በእርድ ፣ በስለት (ነዝር) ፣ ልክ የተከበረውን ካዕባን እንደሚጠውፉት (እንደሚዞሩት) መቃብርንና ጣኦታትን በመጠወፍ (በመዞር) ዒባዳ ያደርጋሉ። ምንም

እንኳን ለበረካ ነዉ ፣ ለተወሱል ነዉ ቢሉም አምልኮ ማለት ግን ይኸዉ ነዉ።

የማያወቀዉ (ጃህሉ) የሕበረተሰብ ክፍል ባለማወቅና የአምልኮን ትክክለኛ ትርጉም ባለመረዳት ሽርክ ዉስጥ ቢወድቅ ባለማወቅ ስለሆነ የተወሰነ ምክንያት ሊኖረዉ ይችላል።

ነገር ግን የአምልኮን ትክክለኛ ትርጉም የሚያዉቁት ትላልቅ ኡለማዎች ምክንያት ምንድን ነዉ? ብዙሐኑ የሕብረተሰብ ክፍል የተዘፈቀበት የቃላት፣ የተግባራትና የእምነት ሁኔታ ከእስልምና የሚያስወጣ ትልቁ የሽርክ አይነት እንደሆነ ጠንቅቀዉ እያወቁ ይህ ተፈላጊዉ የተወሱል አይነት ነዉ ፤ የነቢያት፣ የወሊዮችና የመልካም ሰዎች ውዴታ መግለጫ እንጂ ሽርክ አይደለም ብለው ፈትዋ (ብያኔ) የሚሰጡት ለምንድን ነው?

ከዚያም እነሱ ራሳቸዉ (የነሱን አርአያ በሚከተለዉ በብዙሐኑ ሕዝብ ልብ ዉስጥ ሽርክ እንዲሰርጽ ሽርክ የሆኑ ስራዎችን በመወሊድና ቢድአ በሆኑ አመታዊ በዓላት አማካይነት ይፈጽማሉ።

እነዚህ ሐቅን ደብቀዉ ወደ ኩፍር የሚገፋፉ ኡለማዎች አላህን አይፈሩም ወይ?

ለጥቂት ሳንቲሞችና ጊዜያዊ ለሆነ ስልጣን ሲባል ነዉ ወይ ይህን አስከፊ የሆነ ድርጊት በራሳቸዉና በብዙሐኑ ላይ የሚፈጽሙት?

የዚህ አይነት ኡለማዎች ጠመዉ የሚያጠሙ ናቸዉ።

ውድ አንባቢ ሆይ !

እኔ በሙስሊሙ ላይ ሽርኩል አክበርን በአስፈሪ ሁኔታ የሚያስፋፉትን እነዚህን ተጨባጭ እውነታዎች ስለወቅኩኝ አላህን በመለመንና በሱም ላይ በመመካት እንዲሁም አላህ ሥራዬን እንዲቀበለኝና አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የጠመሙትን ሰዎች አላህ እንዲያስጠቅማቸውም በመፈለግ "ተውሂድን እንዴት ነው የምንረዳው" በሚል ርዕስ ይህንን መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ።

አላህ ከሽርክ ጭለማ ወደ ተዉሂድ ብርሃን ሊያወጣዉ የፈለገዉን ያወጣዉ ዘንድ የበኩሌን አነስተኛ ሙከራ ለማድረግ ፈልጌ ነዉ። አላህ መልካም ዋቢና አጋዥ ነውና። "የጃሂሊያን ምንነት የማያውቁ ሰዎች በኢስላም ውስጥ ሲፈጠሩ የኢስላም ገመድ (ቋጠሮ) አንድ በአንድ መበጣጠስ (መፈታታት) ይጀምራል"

(ኡመር ቢን አልኸጣብ)

አንድ በጣም ሃይማኖተኛ የሆነ ሙስሊም ወንድሜ ነበር። ጥሩ ባህርይ ያለውና የተረጋጋ ሰው ከመሆኑም ጋር ግልፅነቱ ወደር የለሽ ነበር። ሁሌም እንግባባለን እንስማማለን። በአንድ ነገር እንጂ አንለያይም። እሱም በሙታን ሰዎች ወደ አላህ መቃረብ (ተወሱል ማድረግ) ፣ ከአላህ ሌላ እነሱን መጥራት ፣ እነሱን እርዳታ መጠየቅና ለነሱ ማረድና ነዝር ማድረግ ነው እነዚህ ነገሮች በኔና በሱ መካከል ክርክር ያስነሱ ነበር። እንደሌሎቹ ሁሉ ከሱም ንግግር እረዳ የነበረው እነዚህ ነገሮች የተወደዱ ናቸው

ባይባሉም እንኳ ቢያንስ ቢያንስ የተፈቀዱ ናቸው ብሎ እንደሚያምን ነበር፡፡

ከእለታት አንድ ቀን "ከአላህ በስተቀር ሌላ እንደማልጠራና ከሥራዬ ውጭም በሌላ ነገር ወደ አላህ ተወሱል እንደመላደርግ አንተ ታውቃለህ?" አለኝ፡፡ አዎን አውቀዋለሁ ይህም ነው ከአንተ መልካም ነገር እንደጠብቅ ያደረገኝ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ምንም ያልነቁ ሰዎች በቀብር ዙሪያ የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች የሚያመጡት ጥፋቶች እንዳንተ ሕሊና ካለው ሰው ሊሰወሩ አይችሉምና ነው፡፡

## <u>ከአላህ ሌላ ወልዮችን መለመን(መጥራት) ኩፍር ነዉ ወይ?</u>

"ቢሆንም ግን ከአንድ ጊዜ በላይ እንደነገርኩህ እርዳታ ጠያቂዎቹና ተወሱል አድራጊዎቹ እርዳታ የሚጠይቋቸውንና የሚመጀኑባቸው ሰዎች መጉዳት ፣ መጥቀም ፣ መፍጠር ፣ ማስገኘት ፣ ማኖር መግደልና የመሳሰሉትን ከአላህ በስተቀር ሌላ ሊያደርጋቸው የማይችላቸውን ነገሮች ማድረግ ይችላሉ ብለው እስካላመኑባቸው ድረስ ሙታንን በተለይም ወሊዮችን፣ ነቢዮችንና ሷሊሆችን መጥራትና እርዳታ መጠየቅ (ኢስቲጋሳ ማድረግ) ከኢስላም የሚያስወጣ ሽርክ ነው መባሉ እስካሁን አልተዋጠልኝም፡፡" አለኝ፡፡

በዚህ ነገር ላይ ለባርካታ ጊዜያት የተወያየን ቢሆንም ውይይታችን አብዛኛውን ጊዜ አጭርና ጥልቀት ያልነበረው በመሆኑ አንዳችን ሌላውን ማሳመን አልቻለም ነበር፡፡

አንድ ጊዜ "ሰዎች የሚሳሳቱት በግል ስሜታቸው በመመራታቸው ስለሆነ የግል ስሜታችንን ወደጐን ትተን ይህን ጉዳይ በጥናት መልክ ይዘነው ከሁሉም አቅጣጫ በግልጽ ብናየው ምን ይመስልሃል?" አለኝ።

በአላህ ስም እምላለሁ ይህማ ስመኘው የነበረ እድል ነዉ፤ ምክንያቱም ግልጽ ያልሆኑትንና የሚያሣስቱህን ነገሮች ግልጽ ላደርግልህ በጣም እፈልግ ስለነበር ነው። ግራ እንድትጋባና እንድትጠራጠር ያደረጉህም እነዚሁ ነበሩ። ስለዚህ ይህንን አርዕስት በስፋትና በጥልቀት አብረን ብናጠናዉ በጣም ደስተኛ ነኝ። አልኩት።

"በጣም ጥሩ ነዉ" አለና ቀጠል በማድረግ "በዚህ ርዕስ ላይ የናንተ አቋም ምንድን ነዉ? ሙታንን የሚጠሩትን ፣ በነቢዮችና በሷሊሆች መጀን የሚሉትን ለነሱም የሚያርዱትንና የሚሳሉላቸዉን ከእስልምና ይወጣሉ ብላችሁ የምትንተራሱበት ቁልጭ ያለ ማስረጃ ምንድን ነዉ?" አለ

በዚህ ርዕስ ላይ የኛ አቋም የቁርአንን አቋም የሚከተል ነዉ። ይህ የእኛ ፍርድ (ሑክም)፣ እኛ ያመነጨነዉ አስተያየት ወይም የፈጠርነዉ አመለካከት ሳይሆን ከፊቱም ሆነ ከበስተኋላዉ ምንም ዉሸት(ባጢል) ከሌለዉ ከዚሁ ቁርአን የመጣ ነዉ። እኛ ሳንሆን ቁርአን እራሱ ነዉ የመቃብር አምላኪዎችን ካፊሮች ናቸዉ ብሎ የፈረደዉና ሙሽሪኮች ብሎ የጠራቸዉ አልኩት። በተለመደዉ እርጋታዉ "ይህንን ጥቅል የሆነ ቃል መደጋገም አስፈላጊ አይደለም። ይህንማ ስትሉት እንደነበር አዉቀዋለዉ ፤ በኔ አመለካከት

ዝም ብሎ ወሬ ይመስለኛል ፣ ወሬ ደግሞ ያለማስረጃ ተቀባይነት የለዉም። ስለዚህ ግልጽ እና አሳማኝ የሆነ ማስረጃ ምንድን ነዉ? ነገሩ ዝም ብሎ በስሜት የመጣዉን ከመናገር የከበደ እና አደገኛ ነዉ እናንተ በዚህ በችኩልነታችሁና በግዴለሽነታችሁ ሙስሊሞችን ካፊሮች ናቸዉ በማለታችሁ እስከ አሁን ሊገላገሉት ያልቻሉትን ካባድ ፊትና (ዉዝግብ) በሙስሊሞች መሀል ፈጥራችኋል።"

## የቁቡሪዮች ማሳሳቻ

እናንተ ከትልቅ አሳሳች አሉባልታ ወሬ ተጽኖ ስር አልተላቀቃችሁም፣ ይህም ነው እንዳታስተነትኑ መንገዱን የዘጋባችሁና ስለ እኛ የሚታስቡትን እንድታስቡና የምትጠረጥሩትን እንድትጠረጥሩ ያደረጋችሁም። በአጠቃላይ እናንተ ነፃ ሰዎች ናችሁ፣ የኛን ድርጊት ፊትና ወይም ዉዥንብር ወይም ረብሻ ወይም ሌላ ደስ ያላችሁን ብላችሁ መሰየም ትችላላችሁ። ነገር ግን ይህ ሁሉ እንደ ጉህ ብርሃን ከሆነዉ እዉነታ ምንም ነገር መቀየር አይችልም ፣ እሱም እኛ የአላህን ቁርአን አይተን አላህ እንድናስተነትነዉ ባዘዘን መሰረት ያስተነተን ሕዝቦች ነን።

አላህ የቀደሞ ሙሽሪኮችን የገለጸባቸዉን ባህሪ ስናይ ከነዚህ መቃብርን ከሚገዙት፣ ሙታንን ከሚጠሩት፣ በነሱም ከሚመጀኑት ፣ለነሱ ከሚተናነሱትና ከአላህ ጋር በእርድና በስለት ከሚያጋሩት ጋር መቶ በመቶ አንድ ሆነዉ ስናገኘዉ እዉቀታችን የደረሰበትን ለማስጠንቀቅና ግልጽ ለማድረግ

ማንንም አልፈራንም በግልጽ ከመናገርም ወደ ኋላ አላልንም፤ ሰዎች ወደዱትም ጠሉትም አያሳስበንም ገሃድ አወጣነዉ። የሰዎች መዉደድ ወይም መጥላት አንድም ቀን ለሀቅ ወይም ለሐሰት መለኪያ ሆኖ አያዉቅም።

## የሙሽሪኮችና የቁቡሪዮች ማሳሳቻና ማፍረሻዉ

በዚህ ረገድ ለምንለዉና አላህን ለምናመልክበት ማስረጃዉ በሚከተለዉ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ስለሚቀርብ በጥሞና እንድትከታተለው

<u>አንደኛ</u>፦ ሰዎች በአላህ ጌትነት እስካመኑ፣ ያለሱ ፈጣሪ፣ ሲሳይ ሰጪ የሚያኖር፣ የሚገድል የለም ብለው እስካመኑና ከሱ ሌላ የሚጠሯቸው አካለት መጥቀምም ሆነ መጉዳት እንደማይችሉ እስካመኑ ድረስ ሙታንን መጥራታቸውና እርዳታ መጠየቃቸው እንዲሁም አማላጆችና አገናኞች እንዲሆኑላቸው በእርድና በነዝር ወደነሱ መቃረባቸው ከማጋራትም ሆነ ከኩፍር አይቆጠርባቸውም ትላለችሁ።

ነገር ግን ተጨባጩ የሚያሳየው ይህ አስተያየት የተሳሳተ አስተያየት መሆኑንና ይህ አተረጓጐም ከንቱና ሙሉ በሙሉ ከእስልምና መሰረት ጋር የሚቃረን መሆኑን ነው። አላህ ካለ ከሚተከተለዉ ማብራሪያ ግልጽ ሆንልሃል።

## <u>በነቢዮችና በሙሽሪኮች መካከል የነበረው የትግል እውነታ</u>

በነበዮች በተለይም በነብያችን ሙሐመድ (ሰዐወ) እና በቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች መካከል የነበረዉን ትግል በደንብ ያጤነ ሰዉ መረዳት እንደሚችለዉ መንስዔዉ ሙሽሪኮቹ በአላህ መኖር አናምንም ስላሉ እንዳልሆነ ይረዳል።

የትግሉ መንስዔ የሁሉም ነገር ስልጣን በአላህ እጅ እንደሆነ አናምንም ስላሉ አልነበረም፤ ሙሽሪኮቹ የሚጠሩአቸዉን አካላት ከአላህ ጋር በማሻር ጥቅምን ማስገኘት ወይም ጉዳትን መከላከል ይችላሉ ብለው በማመናቸውም አልነበረም። ይልቁንስ እነዚያ ሙሽሪኮች ከነዚህ ሁሉ ነገር እንዱም በልቦናቸው ላይ አርፎ ወይም አስቦውበት አያውቁም።

## ሙሽሪኮች በአላህ ስለማመናቸዉ

ሙሽሪኮች በአላህ መኖርና በጌትነቱ አንድነት ያለምንም ጥርጣሬ ሙቶ በመቶ ያምኑ ነበር፣ አላህ ፈጣሪያቸዉ የሁሉም ነገር ፈጣሪ እንደሆነና ከሱ ሌላ የሚጠሯቸዉ አማልክትና ነቢያት ለራሳቸውም ቢሆን ጥቅምን ማስገኘትም ሆነ ጉዳትን መከላከል እንደማይችሉ እንዲሁም ጥቅምና ጉዳት ፣ ሕይወትና ሞት፣ በአንድ አላህ (ሱ.ወ) እጅ ብቻ እንደሆነና ከፍጡራን ውስጥ ማንም እንደማይጋራው ወይም እንደማያረደው ያምኑ ነበር። የመጀሪያዎቹ ሙሽሪኮች በጌታቸው በአላህ የነበራቸው እምነት ይህን ይመስል ነበር። በአላህ የጌትነት አሐድነት ጥርት ባለ መልኩ ያምኑ ነበር።

የዛሬዎቹ የቀብርና የወሊይ አምላኪዎች ተውሂድ ከቀድሞቹ ሙሽሪኮች ተውሂድ በእጅጉ ያንሳል። ምክንያቱም የአሁኖቹ የቀብርና የወሊይ አምላኪዎች ተናንሰውና እርዳታን በመፈለግ ወደ ሚያመልኳቸው ሙታንና ሌሎች ነገሮች ፊታቸውን የሚመልሱትና ወደነሱ የሚጠጉት በተቸገሩ ጊዜ ነው። ይህ ደግሞ ከመጀመሪያዎቹ ሙሽሪኮች ድርጊት ተቃራኒ ነው። እነሱ በስዕላ-ስዕልና በቅርጻ-ቅርጽ የመሰሉዋቸውን ወሊዮች የሚጠሯቸው ችግር በሌለ ጊዜ ብቻ ነበር። በችግርና ውጥረት ጊዜ የሚጠሩት አላህን ብቻ ነበር። ወደሱ ብቻ ነበር የሚጠጉት። እዚህ ላይ ጓደኞዬ ይህን ሲሰማ በንዴት ቀጣ አለና በጣም አስገራሚና አስደናቂ በሆነ የተቃውሞ አነጋገር "እንዴት? እኮ እንዴት?" አለኝ።

## አቡ ጀህልና አቡለሐብ በአላህ አንድነት የነበራቸው እምነት

አቡጀህል ፣ አቡለሐብና የነሱን እምነት የተከተሉት ሙሽሪኮች ሁሉ የአላህን ጌትነት ፣ ፈጣሪነት፣ ሲሳይ ሰጪነት፣ ሄያወ አድራጊነትና ገዳይነት ፣ጠቃሚነትና ጎጂነት ፣ ያምኑ ነበር። በዚህ ረገድ ምንም በአላህ አያጋሩም ነበር።

"አቡጃህልና አቡለብ ፣ በወሊዮችና በሷሊሆች ተወሰሉ ከሚያደርጉትና ወደ አለህ እነሱን አማላጅ ከሚያደርጉት ሙስሊሞች የበለጠና ጥርት ያለ ኢማን ያላቸው መሆኑ በጣም አሰገራሚና አስደናቂ ነገር ነው።

አቡጀሀልና አቡለሐብ ላኢላሃ ኢለላህ ሙሐመዱን ረሱሉላህ(ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ፣ ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ናቸዉ) ከሚሉት ሙስሊሞች የበለጠ ተዉሂድና የጠራ ኢማን አላቸውን? ሰውየው ምን ነካህ? ምን ማለትህ ነው!? እንዴት እንደዚህ አደገኛ የሆነ ቃል ግልጽ ለማድረግ ቻልክ? ይህና ሌሎች መሰል ንግግሮቻችሁ ድንበር ማለፋችሁን የሚያሳዩ ናቸው። በዓለም ላይ ካሉ በሚሊዮኖች ከሚቆጠሩ ሙስሊሞች ጋር ጠላት ያደረጋችሁ ይህ ነው።" አለኝ።

ይህ አያስገርምም አያስደንቅምም ፣ ሐቂ ግልጽ ብሎ ሲታይ በአላህ ፍቃድ የሚታውቀዉና የሚትቀበለዉ እዉነታ ይኸዉ ነዉ። ማስረጃዎች ግልጽ ብለውና ቀጥ ብለዉ ከፊትህ ሲደረደሩ ነዉ በአላህ ፍቃድ በልብህ ላይ የሚመላለሰዉ የሚወገድልህና ራሳችሁን ከምታሳስቱበትና ማስረጃ ብላችሁ ከምታስቧቸዉ በአእምሮ ላይ ካለዉ ማሳሳቻ የምትላቀቀው።

## ሙሽሪኮች በአላህ አንድነት ስለማመናቸው ማስረጃ

"የኔ ወንድም ማስረጃ እፈልጋለሁ! ለዚህ ለምትሉት ማስረጃችሁ ምንድን ነዉ? የምትሉት ትክክል ከሆነና የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ይህን የመሰለ ኢማን ከነበራቸዉ አላህ ሙሽሪኮች ያላቸዉና በሱ ምክኒያት በእሳት ዉስጥ ዘዉታሪ እንዲሆኑ የወሰነባቸው ሽርክ የተኛዉ ነዉ? አላህ ደማቸዉንና ገንዘባቸዉን ሐላል ያደረገዉና ነቢዩ (ሰዐወ)

አለ።

ከቁርአን ሌላ ለዚህ ነገር ማስረጃ የሚሆነን ምንጭ አለ ወይ? ማስረጃዉ በዚሁ ዘውታሪ በሆነና አንተና ያንተ አይነት አስተሳሰብ ያላቸዉ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ጠዋትና ማታ በምታነቡትና አላህን በምታመልኩበት ኪታብ ዉስጥ ነዉ። እናንተ ግን ስታነቡት አትመረምሩትም፤ አትረዱትምም።

## <u>ሙሽሪኮች አላህ ብቸኛ ፈጣሪ፣ ሲሳይ ሰጪ፣ ሕይወት ሰጪና ሕይወት ነሺ መሆኑን ስለመቀበላቸዉ</u>

አላህ (ሱ.ወ) የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች እሱ ፈጣሪያቸዉ፣ ሕይወት ሰጪና ነሺ፣ ጠቃሚና ጉጂ መሆኑን ማመናቸዉን ሲያረጋግጥ ለነቢዩ (ሰዐወ) እንዲህ አላቸዉ፡-

وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ
لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ فَأَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ

"ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ፀሐይንና ጨረቃንም ያገራ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል ፤ ታዲያ እንዴት ይመለሳሉ?"

(አል-ዐንከቡት 29:61)

وَلَئِن سَأَلْتَهُم
مَّن نَّزَّلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَحْيَا بِهِ ٱلْأَرْضَ مِنۢ بَعْدِ مَوْتِهَا

لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۚ قُلِ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ ﴿٦٣﴾

"ከሰማይም ውሃን ያወረደና በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ያደረጋት ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው አላህ ነው ይሉሃል ፡ ምስጋና ለአላህ ነው በላቸው ፡ ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።" (አል-ዐንከቡት 29:63)

قُل لِّمَنِ ٱلْأَرْضُ وَمَن فِيهَآ إِن
كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٨٤﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِ ۚ قُلْ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ
﴿٨٥﴾ قُلْ مَن رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ ٱلسَّبْعِ وَرَبُّ ٱلْعَرْشِ ٱلْعَظِيمِ
﴿٨٦﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِ ۚ قُلْ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴿٨٧﴾ قُلْ مَنۢ بِيَدِهِۦ
مَلَكُوتُ كُلِّ شَىْءٍ وَهُوَ يُجِيرُ وَلَا يُجَارُ عَلَيْهِ إِن
كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٨٨﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِ ۚ قُلْ فَأَنَّىٰ تُسْحَرُونَ ﴿٨٩﴾

"ምድርና በውስጥዋ የለው ሁሉ የማን ነው? የምታውቁ ብትሆኑ (ንገሩኝ) በላቸው። በእርግጥ የአላህ ነው ይሉሃል፤ ታዲያ አትገሰፁም? በላቸው። የሰባቱ ሰማያትና የትልቁ ዙፋን (ዐርሽ) ጌታ ማነው በላቸው። በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፤ እንግዲያ አትፈሩምን? በላቸው። የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የሆነ እርሱ የሚጠብቅ በርሱ ላይ የማይጠበቅ ማንነው? የምታውቁ እንደሆናችሁ (መልሱልኝ) በላቸው። በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል ታዲያ እንዴት ትታለላላችሁ? በላቸው። (አልሙእሚኑን 23:84-89)

مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ أَمَّن يَمۡلِكُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَمَن يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ ٱلۡمَيِّتِ وَيُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتَ مِنَ ٱلۡحَيِّ وَمَن يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَۚ فَسَيَقُولُونَ ٱللَّهُۚ فَقُلۡ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴿٣١﴾

"ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተነብርስ ማን ነው? በላቸው ፤ በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል ፤ ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ?) አትፈሩምን? በላቸው።" (ዩኑስ 10:31)

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የአላህን መኖር የማይክዱ መሆናቸዉንና ለአላህ አጋር እንደሌለዉና ብቸኛና በስልጣኑ ማንም እንደማይገባበት እንደሚያምኑና፣ የጌትነት አሀድነቱን ሙሉ በሙሉ እንደሚቀበሉ የሚያረጋግጠዉ ማስረጃችን ይህ ነዉ። ስለዚህም እነሱ (የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች) ሕይወትን እንዲሰጧቸው ወይም ሞትን እንዲከላከሉላቸው ወይም ዝናብን እንዲያዘንቡላቸው ወሊዮቻቸውን ሲለምኑ በእውነት የሚጠሩት ወደ ወሊዮቻቸው አለመሆኑን ከዚህ በትክክል ማረጋገጥ ይቻላል።

ደስታን እንዲሰጧቸው ወይም ሐዘንን እንዲያስወግዱላቸው ከወሊዮች አማልክት ናቸው ብለው ወደ ያዟቸው ጣዖታት አይቃረቡም ነበር። ከነዚህ የቁርአን አንቀጾች እንደምንረዳው ይህ ሁሉ ሊሆን የሚችለው የሁሉም

ነገር ሥልጣን በእጁ በሆነው በአላህ ብቻ መሆኑን በእርግጠኝነት እያመኑ ይህን የመሰለ ነገር እንዴት ሊያደርጉ ይችላሉ? (ወደ አማልክቶቻቸው እንዴት ይቃረባሉ?)

በዚህ ግልጽ በሆነ ማስረጃ መሰረት ልክ እንደ አላህ ጥቅምም ሆነ ጉዳት ... ባት በእጁ ነው ብሎ እስካላመነ ድረስ ከአላህ ሌላ የሚጠራ ሰው ሙሽሪክ አይሆንም ብላችሁ የያዛችሁት ደካማ መስፈርት ከንቱ መሆኑ ግልጽ ይሆንላችኋል።

ይህ መስፈርታችሁ ትክክል ቢሆንና የምትሉት ነገር በኢስላማዊ አመለካከት ጤናማ ቢሆን ኖሮ በአቡለሐብና በአቡጃህል እንደዚሁም በሕዝቦቻቸዉ ላይ አላህ ሙሽሪኮች ናቸዉ ብሎ ባልፈረደ ነበር። ምክኒያተም እናንተ የምትሉትን መስፈርት ያሟሉ ነበረና። አላህ ማድረግ ይችላል ብለው በሚያምኑት መልኩ እነዚህ የሚጠሯቸው ጣዖታት መጥቀምም ሆነ መጉዳት ይችላሉ ብለው አያምኑም ነበር ከላይ በተጠቀሰው አ... ቁርአን በግልጽ አስቀምጦታል።

## የቀደሞዎቹ ሙሽሪኮች ኢማን ከዛሬዉ ዘመን

## ሙሽሪኮች ኢማን ይበልጥ ነበር።

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ተወሂድና በጌታቸው ላይ ያላቸዉ እምነት ከዛሬ ዘመን የመቃብር አምላኪዎች ተዉሂድና እምነት የጠነከረ ለመሆኑ ፣ ማስረጃዉ ከዚሁ የማያልቅ ክምችትና የማይደበዝዝ ብርሃን ከሆነዉ ቁርአን

ነዉ:: አላህ (ሱ.ወ) እነዚያን ሙሽሪኮች አስመልክቶ እንዲህ ይላል:-

فَإِذَا رَكِبُوا۟ فِى ٱلْفُلْكِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ ﴿٦٥﴾

"በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው ይጠሩታል ወደ የብስ (በማውጣት) በዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ::" (አል-ዐንከቡትን 29:65)

وَإِذَا مَسَّكُمُ ٱلضُّرُّ فِى ٱلْبَحْرِ ضَلَّ مَن تَدْعُونَ إِلَّآ إِيَّاهُ فَلَمَّا نَجَّىٰكُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ أَعْرَضْتُمْ وَكَانَ ٱلْإِنسَٰنُ كَفُورًا ﴿٦٧﴾

"በባህሩም ውስጥ ጉዳት ባገኛችሁ ጊዜ የምትጠሯቸው (አማልክት) ሁሉ ከርሱ (ከአላህ) በቀር ይጠፋሉ ፤ ወደ የብስም በማድረስ በዳናችሁ ጊዜ (እምነትን) ትተዋላችሁ ሰውም በጣም ከሐዲ ነው::" (አል-ኢስራእ 17:67)

قُلْ مَن يُنَجِّيكُم مِّن ظُلُمَٰتِ ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ تَدْعُونَهُۥ تَضَرُّعًا وَخُفْيَةً لَّئِنْ أَنجَىٰنَا مِنْ هَٰذِهِۦ لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّٰكِرِينَ ﴿٦٣﴾ قُلِ ٱللَّهُ يُنَجِّيكُم مِّنْهَا وَمِن كُلِّ كَرْبٍ ثُمَّ أَنتُمْ تُشْرِكُونَ ﴿٦٤﴾

"ከየብስና ከባህር ጨለማዎች (መከራዎች) በግልጽና በምስጢር የምትጠሩት ስትሆኑ ከነዚህ (ጨለማዎች)

ቢያድናን በእርግጥ ከአመስጋኞች እንሆናለን (ስትሉ) የሚያድናችሁ ማነው? በላቸው። አላህ ከሷና ከጭንቅም ሁሉ ያድናችኋል፤ ከዚያም እናንተ ታጋራለችሁ በላቸው።"
(አል-አንዓም 6:63-64)

እነዚህ የቁርአን አያዎች ሙሽሪኮቹ በመርከብ ሲጓዙና ለችግር ተጋልጠዉ በአደጋ ላይ መዉደቃቸዉን ሲገነዘቡ ወልዮችም ይሁኑ ሌሎች አማልክቶቻቸውን ይከዱና እምነትን ለአንድ አላህ ብቻ አጥርተዉ ወደሱ ይዞራሉ ፤ ተስፋቸዉንም በሱ ላይ ብቻ ያደርጋሉ። ምክኒያቱም ከአላህ ሌላ የሚጠሯቸዉ ጣኦታት በዛች አስጨናቂ በሆነች ቅጽበት ምንም አይነት እርዳታና እገዛ ሊያደርጉላቸዉ የማይችሉ ደካሞች መሆናቸዉን ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ። እንዲያዉም ከአላህ ሌላ የሚጠሯቸዉ ጣኦታት እንኳንስ ሊደርሱላቸዉ የጥሪያቸዉንም ድምፅ እንደማይሰሙ በደንብ ያዉቃሉ።

ስለዚህ የሚያሳስቁና የሚያጭበረብሩ ሽፍኖች በዛች ወሰኝ ሰዓት ከፊታቸዉ ብጥስጥስ ብሎ ይጠፉና ሀቁ ግልጽ ብሎ ይታያቸዋል። እሱም ከአላህ ሌላ ማንም ይሁን ምን በዛች አስጨናቂ ወቅት ሊጠሩትና ሊጠጉት እንደማይገባ ግልጽ ይሆንላቸዋል።

## የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች በችግር ጊዜ አማልክቶቻቸዉን ረስተዉ ወደ ፈጣሪያቸዉ የሚመለሱት እንዴት ነው?

አንድ አላህ (ሱወ) ብቻ ከመስጠም የሚያድናቸዉ መሆኑን እርግጠኛ በመሆናቸዉ ወደ አላህ በመመለስ እምነትን ለሱ ብቻ ጥርት አድርገዉና ተናንሰው ይለምኑታል። እርዳታና ስጦታ ከሱ ብቻ ይፈልጋሉ። በሰላሙ ጊዜ አማልክት አድርገዉ የያዙዋቸዉን ወልዮች ይረሣሉ። ቁርአን እንደመሰከረላቸው እነዚያ ሙሽሪኮች በአደጋ ክልል ውስጥ እስካሉ ድረስ እምነትን ለአንድ አላህ ብቻ ጥርት ያደርጋሉ። ነገር ግን ከአደጋ ስፍራ እልፍ ካሉና ወደ ምድር በደረሱ ጊዜ ከአባቶቻቸዉ የወረሱት ባህል መልሶ ይወስዳቸዋል፤ ከአላህ ጋር ሌላዉን በዱአ በእርድና በስለት ያጋራሉ። ለዚህ ነዉ አላህ የወቀሳቸዉና ሙሽሪኮች ብሎም የጠራቸዉ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ

"ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወድያውኑ እነሱ ያጋራሉ።"

አንድ ችግር ሲደረስባቸውና አደጋ ሲያጋጥማቸው እምነትን ለአላህ ብቻ በማጥራትና ወደሱም ብቻ በዱዓ በመመለሰ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ሁኔታ ይህን ይመስል ነበር።

## የዛሬዎቹ ሙሽሪኮች እንዴት በችግር ጊዜ ፈጣሪያቸዉን ረስተዉ ወደ ወሊዮቻቸዉ ይሮጣሉ?

የዛሬዉ ዘመን ቀብር አምላኪ ሙሽሪኮች ከቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ተቃራኒዎች ናቸዉ። አላህን የሚለምኑትና የሚጠሩት በሰላሙ ጊዜ ብቻ ነዉ።

ችግር ሲጠናባቸዉና የመዉጫ ቀዳዳ ሲጠፉቸዉ ግን አላህን (ሱወ) ይረሱና ወሊዮቻቸዉን ያስታዉሣሉ በመጨነቅና በመጠበብ ይጠሯቸዋል። በእርድ ፣ በስለት ፣ በመፍራትና በመተናነስ ወደነሱ ይቃረባሉ።

በደዊ፣ ጀይላኒ፣ ረፋዒ፣ ቲጃኒ፣ ዐይደሩስ፣ ኢብን ዒሣና ሌሎችም ወልዮች ሞቅ ያለ ጥሪና ጥርት ያለ ዱዓእ በስማቸዉ ሲደረግ የምትሰማዉ በችግር ጊዜ ብቻ ነዉ።

ቁቡሪዮች (የመቃብር አምላኪዎች) በባህር ሲጓዙ አደጋ ካጋጠማቸዉ አላህን(ሱ.ወ) ረስተዉ ወሊዮቻቸዉን በማስታወስ በልመና ያጣድፉሉ ፣ ከነሱ እርዳታን ይጠይቃሉ፣ በመጨነቅና በመተናነስ እርዳታህን ስጠን ያበደዊ፣ ያጀይላኒ ረፋዒ ወዘተ . . . ይላሉ። ስታያቸዉ ልክ አጠገባቸዉ ሆነዉ የሚያናግሯቸዉ ይመስሉሃል።

ከመስጠም ከዳኑ ለሚያመልኳቸው ቀብሮች ስለትና ቁርባን ለማቅረብ በመጨነቅ ፣ በመረበሽ ፣ በመተናነስና በመዋረድ ቃል ሲገቡላቸው ብታያቸው ሽርክ ወይም ኩፍር ምን ያክል ቅሌት እንደሆነ ፣ የሰውን ልጅ ክብር እንዳሰጣና

እንዳዋረደው ማሰብ ከሚችለው የሰው ልጅ ደረጃ ሣር ከሚግጠው ከብት በታች እንዳወረደው ታያለህ።

የሰው ልጅ የሚሰማውን፣ የሚያየውንና ከሱ ጋር የሆነውን ፈጣሪውን፣ ሲሳይ ሰጪውን፣ ጌታውን ከልቡ ትቶ ምንም ወደ ማይጠቅመው ለራሱም በመቃብሩ ውስጥ ሥጋውን ከአጥንቱ ለመግፈፍ የሚረባረቡበትን ትላትል ከራሱ መከለከል ወደ ማይችለው ወደ በሰበሰው አጥንት በልቡ በመዞር ለርሱ በመተናነስና በመዋረድ ከርሱ እርዳታ ከመጠየቅና ከመስጠም እንዲያድነው ከመለመን የበለጠ ውር ደትና ዝቅጠት ምን አለ? አላህ እንዲህ ይላል:-

وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن
لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَـٰمَةِ وَهُمْ عَن دُعَآئِهِمْ غَـٰفِلُونَ ﴿٥﴾

"እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስም ለርሱ የማይመልስለትን (ጣዖት) ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማንነው ? እነርሱም ከጥርያቸው ዘንጊዎች ናቸው:"
(አል-አሕቃፍ 46:5)

የዚህ አይነቱ የመጃጃል ድርጊት ብዙ ጊዜ አጋጥሞኝ የጃሂሊያ ድርት በሆነዉ በዚህ የሽርክ አይነት ሞራሌ ተነክቶ ልቤም በጣም አዝኖዋል።

## የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ቁቡሪዮች ሊሰጥሙ ሲሉ እንዴት ሊጋጠማቸው ቻለ?

ከዛሬ 25 አመት በፊት በቀይ ባህር ላይ በመርከብ ስንጓዝ ወልዮቻቸዉን ተጨንቀዉ ሲለሚኑ ብዙዎች አጋጠመዉኛል።

በአንዲት ትንሽ መርከብ ከሰማንያ ሰው በላይ ሆነን በመጓዝ ላይ እያለን፣ ማዕበል ከየአቅጣጫው ተነስቶ ሲከበን መርከቧ በማዕበሉ ተመታ ልትሰጥም ቀረበች ፣ አንዳንዴም ከግፊቱ የተነሳ ባህሩን ለቃ የሚትበር ትመስላለች።

በዚች አስጨናቂ ወቅት የመቃብር አምላኪዎች እርዳን፣ ጠብቀን፣ አድነን ሲሉ ተንጫጩ። ታዲያ አድነን የሚሉት ምንም የማይሣነዉን ሕያውን አንድ አላህን ሣይሆን ምንም የማይችለዉን የመቃብር ነዋሪን ነዉ።

ፍርሃትና እዝነት በተሞላበት ልቡና ከዛሬ ስድስት መቶ አመት በፊት ከዚህ አለም በሞት የተለየውን ሰኢድ ኢብን ኢሣን (አላህ ይዘንላቸውና) መጣራት ጀመሩ። (የኢሣ ልጅ ሆይ፦ የኢሣ ልጅ ሆይ፦ የዲን ምሰሶ የሆንክ ሆይ) እያሉ ተስፋ በተቀላቀለበት ድንጋጤ መጣራት ጀመሩ። ልክ የነሱ መትረፍና መስጠም በአላህ እጅ ሣይሆን በሱ እጅ ያለ ይመስላል ከመስጠም ካተረፍከን እንዲህ ያለ ነገር መቃብርህ ዘንድ እናመጣለን እያሉ በስለት መሸቀዳደም ጀመሩ።

## ቁቡሪዮቹ የዚህን መጽሐፍ አዘጋጅ ባህር ውስጥ ሊጥሉት ቀረቡ

በዛን ወቅት እድሜዬ ትንሽ ከመሆኑም ጋር አንድ ሙስሊም በዚህ አይነት ወቅት ከአላህ ሌላ ማንንም መጥራት ተገቢ እንዳልሆነና እምነትን ለርሱ ብቻ በማጥራት በመተናነስና በዱዓእ ወደ አላህ ብቻ እንዲመለሱና እንዲጠጉ፣ እንኳንስ ለጥሪያቸው መልስ መስጠት ይቅርና ጥሪያቸውንም መስማት የማይችለውን፣ ምንም ነገር በእጁ የሌለውን፣ ሼክ ኢብኑ ዒሳን እንዲተው በትህትናና በርኅራሄ ላሳምናቸው ስሞክር ወሃቢ! ወሃቢ! እያሉ ሁሉም ይጨሁብኝ ጀመሩ። አላህና ከአላህ በኋላ ደግሞ እምነታቸዉን ደብቀዉ በመርከቧ የሚጓዙት አንዳንድ ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ በዚያ ማዕበል ዉስጥ ወርዉረዉ ሊጥሉኝ ነበር።

በኢብን ኢሣ ሣይሆን በአንዱ አላህ ችሮታ ብቻ ከዚህ አደጋ ተረፍን ፤ ሁሉም ነገር ሲረጋጋ እርስ በርሳችን የእንኳን አተረፈህ የደስታ መግለጫ መለዋወጥ ስንጀምር በዚያች አስጨናቂና አደገኛ ወቅት አድባሩ(ቁጥብ) ኢብን ኢሣ ባይኖርና ባይደርስልን ኖሮ ሁላችንም የአሣ እራት በሆን ነበር እያሉ በመመፃደቅ በወሊዮች ላይ መጥፎ አስተያየት አለህ እያሉ ያስፈራሩኝ ጀመር።

## ወሊዮች በችግር ጊዜ ይደርሳሉ የሚለዉ አጉል እምነት

ይህን ግልጽ የሆነ ኩፍር (ክህደት) መስማት ራሴን አሣምሞኛል እናንተ ራሣችሁን እየበደላችሁ ነዉ፣ በሼክ

ኢብን ኢሣ ላይ(ረ.ሁ) የፈጠራ ወሬ አያወራችሁ ነዉ አልኳቸዉ።

እናንተ የሚትጠሩት በህይወት የሌለዉ ሼክ ፣ እንኳንስ በዚህ ማዕበል ዉስጥ መጥቶ ሊያድናችሁ ቀርቶ ጥሪያችሁንም መስማት አይችልም።

እናንተ ሰዎች ሆይ! ልብ በሉ ፣ ይህ ከአላህ ሌላ የምትጠሩት በሕይወት የሌለ ሰው ነዉ ፤ የሞተ ሰው ደግሞ እንደማይሰማ አላህ አረጋግጦልናል። ቁርአንም ይህን ሲያፀድቅ እንዲህ ይላል፡-

إِنَّكَ لَا تُسْمِعُ ٱلْمَوْتَىٰ وَلَا تُسْمِعُ ٱلصُّمَّ ٱلدُّعَآءَ إِذَا وَلَّوْا۟ مُدْبِرِينَ ﴿٨٠﴾

"አንተ ሙታንን አታሰማም ፤ ደንቆሮችንም የሚተው ሆኖ በዞሩ ጊዜ ጥሪን አታሰማም።" (አል-ነምል 27:80)

وَمَا يَسْتَوِى ٱلْأَحْيَآءُ وَلَا ٱلْأَمْوَٰتُ ۚ
إِنَّ ٱللَّهَ يُسْمِعُ مَن يَشَآءُ ۖ وَمَآ أَنتَ بِمُسْمِعٍ مَّن فِى ٱلْقُبُورِ ﴿٢٢﴾

"ሕያዋንና ሙታንም እኩል አይሆኑም ፤ አላህ የሚሻን ሰው የሰማል። አንተም በመቃብር ውስጥ ያሉትን አሰሚ አይደለህም።" (ፋጢር 35:22) [1]

---

[1] ማንኛውም የሞተ ነገር የማይሰማ መሆኑ አጠቃላይ የሆነ፣ የፀናና የማይለወጥ የተፈጥሮ ሕግ (አላህ በፍጥረታቱ ላይ የወሰነ ሕግ ነው።) በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ሊሰሙ እንደሚችሉ የተለየ ማስረጃ የደረሰን ብቻ ሲቀር ሌላው አይሰማም። አጠቃለዩ ሕግ እንዳለ ሆኖ ይህ የተለየ (ኹሱስ) ነው። ታዲያ ሙታን ወሊዮቻቸው ጥሪያቸውን እንደሚሰሙላቸው እነዚህ ቁቡሪዮች ማስረጃ ከየት አገኙ? ሸይኽ እገሌ፣ እገሌ፣ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ቦታ ቢጠራው ሊሰማው እንደሚችል በማድረግ አላህ ከሌሎች ሙታኖች የተለየ ያደረገው=

ነገር ግን እናንተ የአላህን ሕግጋት ባለማወቃችሁና በቁርአን ዉስጥ የተገለፀዉን ማስተንተንና መረዳት እምቢ በማለታችሁ፣ ይህን የመሰለ የጅል ስራ ትሰራለችሁ። ምን ጊዜም ከናንተ ጋር የሆነውንና የሚሰማችሁን፣ የሚያያችሁን፣ ምንም የማይሳነዉን ትታችሁ የማይሰማችሁንና የማያያችሁን በሕይዎት የሌለዉንና ስለእናንተ ምንም የማያዉቀዉን ትጠራላችሁ።

ከዚህ አደጋ ለመትረፋችን ኢብን ኢሣም ሆነ ሌላዉ ምንም አስተዋጽኦ የላቸዉም። ከነቢዮች እርዳታን መፈለጋችሁና ሷሊሆችን መጥራታችሁ ምንም ሣይበግረዉ በችሮታዉና በእዝነቱ ምንም የማይሳነዉ አንድ አላህ ብቻ ነዉ የተረፈን። ከነቢያትም ሆነ(ዐሰወ) ከሷሊሆች (ረዐ) በዛች አስጨናቂ ሰአት አንዳቸዉም ከኛ ጋር አልነበሩም። ብቻዉን ከኛ ጋር የነበረዉ አንድና ብቸኛው በባህርና በየብስ የሚያንቀሳቅሰን አላህ ብቻ ነዉ።

አንዱ ሲፈላሰፍ፡ "አላህ ከሁሉም በላይና ሁሉም ነገር በሱ እጅ መሆኑን አንክድም" አለ።

ይህ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ይሉት የነበረ ያረጀ ያፈጀ አባባል ነዉ። እንደዚሁም ተግባርህ ቃልህን ይቃረናል። በምትለዉ ነገር ከልብህ የሚታምን ብትሆን ኖሮ ፣ በጭንቅና በመከራ ወቅት ከሐያሉ ፈጣሪ ወደ ደካማና ሟች ፍጡር

=ለመሆኑ በቁርአን ተነግሯልን? ይሰማሉ በባል እንኳ ሰዎች ከአላህ ሌላ እነሱን እንዲጠሩና ከነሱ እርዳታን እንዲጠይቁ አላህ ፈቅዷልን? ለጥሪያቸው መልስ እንደሚሰጡና እርዳታ ሲጠይቋቸው እንደሚረዷቸውና እንደሚያድኗቸው አላህ ተናግሯልን? ይህ ነገር እስከሚቀሰቀሱበት እለት ድረስ መልስ ያላገኘ ጥያቄ ሆኖ ይቆያል

ባልዞርክ ነበር። እንደ ተዘገበዉም በችግር ጊዜ እምነትን ለአንድ አላህ ጥርት ከሚያደርጉት የቀድሞቹ ሙሽሪኮችም ያነሰና ደካማ ኢማን ያለው ሰው ሆንክ። አልኩት።

## ሸይጣን ለቁቡሪዮች (የመቃብር ተገዢዎች) እንዴት ከወሊዮቻቸው ጋር ይመሳስልባቸዋል? (ከወሊዮቻቸው ጋር ተመሳስሎ እንደሚታያቸው)

አንደኛዉ ማስረጃ ያገኘ ይመስል፡- "አንተ ወሊዮችን ስለምትጠላና ከራማቸዉን ሰለማትቀበል በዛች አስጨናቂ ወቅት እኛ ያየነዉን ነገር እንዳታይ ተደርገሃል።" አለኝ።

ወሊዮችን እንደማልወድና ከራማቸዉን እንደማልቀበል ማን ነገረህ? ከአላህ ወሊዮች አንዱን ወሊይ ስሰድብ ሰምተህኝ ታዉቃለህ? ወይም ከሙእሚን ሷሊሆች አንዱን ሣናንቅ አይተህኝ ታዉቃለህ? በቁርአንና በሐዲስ የተረጋገጠዉን አላህ ከወሊዮቹ ለአንዱ የሰጠዉን ከራማ አልቀበልም ስል ሰምተህኝ ታዉቃለህ ወይ?

አላህ ለዋሻ ሰዎች የሰጣቸዉንና ዋሻዉ ከተደፈነ በኋላ ቋጥኙ ፈቀቅ ብሎ ዋሻዉ የተከፈተላቸዉን ከራማ አልቀበለልም ሲል ሰምተህኝ ታዉቃለህ ወይ?

በሐዲስ የተረጋገጠዉን የአቡበከር ፣የዑመር፣ የዑስማን፣ የዓሊይና የሌሎችን ሰሐቦች (ረ.ዐ) የአላህ ወሊይነታቸውና

በጀነት መበሰራቸውን አልቀበልም ስል ሰምተህኝ ታዉቃለህ ወይ?

ወይስ በሐሣባችሁ የማይስማማዉን፣ የተሳሳተ መንገዳችሁን የማይቀበለዉን፣ በአጉል እምነታችሁ (በኹራፋታችሁ) የማያምነውንና ስትሣሣቁ ዝም የማይላችሁን ሰው የምትወነጅሉበት የተለማደው የዘወትር ውንጀላችሁ ነው?

ነገር ግን በዛች ቀዉጢ ሰዓት ያያችሁትና እኔ አይቼው እንዳልጠቀምበት አላህ የነፈገኝ ነገር ምንድን ነዉ? በል እስቲ ንገረኝ። አልኩት

"ታላቁን አድባር (ቁጥብ) ሼክ ሰኢድ ኢብን ዒሣን የብርሃን ቺቦ መስለዉ የመርከቧን ምሰሶ (ደቀል) ይዘዉ ባህሩ እንዲረጋ ሲያነጋግሩት አየናቸዉ። በርግጥም ባህሩ ከነበረበት አደገኛ ሁኔታ ፀጥ አለ በዚህ በታላቅ አድባር በረከት ተረፍን።" አለ።

በማፌዝ፦ ከዛሬ ስድስት መቶ አመት በፊት የሞተዉን ሼክ ሰኢድ ኢብን ኢሣ አል አሙዲን ታዉቃቸዉ ኖሮዋል እንዴ? አልኩት። "በርግጥ አላዉቃቸዉም።" አለ።

ቀደም ሲል ካላየሀቸው ከመርከቧ በላይ ሆኖ ባህሩ ፀጥ እንዲል ትእዛዝ ሲያስተላልፍ ያየሄው ነገር ሸህ ሰኢድ ኢብን ኢሣ አልዐሙዲ መሆናቸውን እንዴት አወቅክ? ያየሄው ነገር አለ እንበልና ይህ ያየሄው ነገር ሸህ ኢብን ኢሣ መሆኑን የሚያረጋግጥልህ ወህይ ከሰማይ ወርዶልሃል ወይ? ስለዉ ግራ ተጋባ መልስም አጣ።

## በጨለማ ተዋጠ ፣ ኢብን ኢሣ ከሱ ጋር እንዳለ አድርጉ ወሰደ

በእዉነት ኢብን ኢሣንም ሆነ ሌላዉን ከመርከቡ ምሶሶ ላይ ሆነዉ አላየሁም። ባይሆን በፍርሃትና በጭንቀት ወቅት የተዋጥከበት ጭለማ ከሸይጣን ጋር በመተባበር ኢብን ኢሣን መሰሉህ ፣ በጥመትህ እንድትገፋበትና የባሰ ከመንገድ እንድትርቅ አደረጉህ። አልኩት።

ብቸኛዉና ክርክራችንን ያቋረጠበት አስገራሚ መልሱ ወሐቢ፣ ከሐዲ፣ ዚንዲቅ ብሎ መጮህ ነበር። ይህ ደግሞ በአሣማኝ ማስረጃ ሲሸነፉ የሚጠቀሙበት የመጨረሻ መሣሪያቸው ነው።

በዚህን ጊዜ አሁንስ ምን አስተያየት አለህ?

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች በችግር ጊዜ በፈጣሪያቸዉ ላይ ያለቸዉ እምነት ከመቃብር አምላኪዎች ኢማን የበለጠ ጠንካራ መሆኑን ከዚህ ከተናገርኩት ዉስጥ የሚያሳምንህ ነገር አላገኘህምን? አልኩ ለጓደኛዬ።

## የመቃብር አምላኪዎች ማሣሣቻዎች

"አንተም እንዳልከው እነዚህ የመቃብር አምላኪዎች በዛች አስጨናቂ ሰዓት ኢብን ዒሣን ሲጠሩና እርዳታን ሲጠይቁ ፣ በአላህ ሣይተማመኑ ቀርተዉና ኢብን

ዒሣም ሆነ ሌሎች ከአላህ ዉጪ የሚጠሩዋቸዉ በየብስና በባህር ያንቀሣቅሱናል ወይም ደግሞ ልክ አላህ ጥሪያቸዉን እንደሚሰማና እደሚደርስላቸዉ እነሱም ይሰሙና ይደርሱልናል ብለዉ ሣይሆን በነዚህ ወሊዮች በረካ ተወሱል በማረጋቸው አላህ (ሱ.ወ) ያድነናል ብለው ነው። በዛች አስጨናቂ በሆነች ሰዓት የነዚህን ሰዎች ጥገኝነት የጠየቁትና በነሱ ስም የጮሁት እነዚህ ሰዎች አላህ ዘንድ ክብር አላቸው አላህ ደግሞ ፍርሐትና ሐዘን በሌለባቸው ወልዮች ሲል ያድነናል ብለው ነው። ይህ መሆኑ እየታወቀ እነዚህን ሰዎች ሙሽርኮች ብለህ ስትጠራቸውና ኢማናቸውና ተውሂዳቸው ከቀድሞቹ ሙሽረኮች ያነሰ ነው ስትል በጣም ድንበር አልፈህባቸዋል።" አለኝ።

ይህቺማ ያረጀችና ያፈጀች ማሳሳቻ ነች ፣ በብዙ መልኩ አእምሮው ጤነኛ በሆነ ሰው ዘንድ ልትሰራ አትችልም። አልኩት።

ምክንያቱም እነዚህ የመቃብር አምላኪዎች በሕይወት የሌሉትን ወሊዮች በሐዘንም በደስታም ከነሱ ጋር እንደሆኑና፣ ጥሪያቸዉን ሰምተዉ መልስ እንደሚሰጡዋቸዉና፣ የማዳን ችሎታ አላቸዉ፣ ብለዉ ባያምኑ ኖሮ እንደዚህ ባልጮሁባቸዉ ነበር። ልክ ደካማውና ምንም ነገር የማይችለው፣ ጠንካራውንና በሁሉም ነገር ላይ ችሎታ ያለውን እርዳታ በሚጠይቅ መልኩ ተዋርደውና ተናንሰው ባልለመኗቸው ነበር። ከመስጠም ያዳኗቸው እንደሆነ እያሉ የተለያዩ ስለቶችን ባልተሳሉላቸውና ቁርባኖችን ለማቅረብ

ቃል ባልገቡላቸው ነበር። እንዲያውም በፍላጉትና በጉጉት ስለቶቻቸውን ባለደረሱ ነበር።

አንድ ማሰብ የሚችልና ጤናማ አእምሮ ያለዉ ሰዉ እንደማይሰማው፣ እንደማይደርስለት፣ እንደማይጠቅመውና እንደማጉዳው የሚያውቀውን ነገር እንድረዳውና እንዲደርስለት ይጠራዋል ተብሎ ይታሰበልን?

## በሕይወት የሌሉትን ወሊዮች መለመን ኩፍር ወይም እብደት ነዉ።

በሕይወት የሌሉትን ወሊዮች የሚጠሩት በሁለት ነገሮች መካከል ናቸዉ። ወይ በሕይወት የሌሉት ወሊዮች (በየትኛዉም ርቀት ሆነዉ) ይሰሙናል፣ ይደርሱልናል፣ ያድኑናል ብለዉ ያምናሉ ወይም ደግሞ አያምኑም። በዚህ አይነት መልኩ የሚያምኑ ከሆነ ይህ ትልቁ ሽርክና አላህ ምህረት የማያደርግለት ነው።

ወይም ደግሞ እነዚህ በሕይዎት ሣይኖሩ የሚጠሩዋቸዉ ሰዎች አይሰሙም፣ አያድኑም ብለዉ ያምናሉ። አይሰሙም፣ አይጠቅሙም እያሉ መጥራታቸዉ ደግሞ እብደት ነዉ። እብድ ደግሞ በሐይማኖታዊ ተግባራት ላይ ግዴታ የለበትም። ስለዚህ እነዚህ የመቃብር አምላኪዎች ሙሽሪኮች ወይም እብዶች ስለሆኑ በፈለገዉ ልትፈርጃቸዉ ትችላለህ።

ሐቁ ግን፣ የመቃብር አምላኪዎች እብዶች ሳይሆኑ ሽይጣን የሽርክ ተግባራትን አጋጦ እያስወደዳቸዉና

እያሣሣታቸዉ ፈተና ዉስጥ የከተታቸዉ ሰዎች ናቸዉ። ምንም ከማይሣነዉ አላህ ይልቅ በወሊዮቻቸዉ ችሎታ ባይተማመኑ ኖሮ፣ አላህን ትተዉ በህይወት ወደሌሉት ሙታን ወሊዮቻቸዉ በመተናነስ፣ በመዋረድና በፍርሃት ባልዞሩ ነበር።

ከዚህ የከፋ ኩፍርና ምንስ ጥመት አለ? እንደዚህ አሣምሮ ለፈጠራቸዉ አላህስ ምን አስቀሩ?

ከጓደኛዬ ጋር ስንከራከር እዚህ ደረጃ ላይ ከደረስን በኋላ ግራ በመጋባት "ግን … ግን… አለና አመነታ። ከዚያም ያሰበዉን መናገር አቅቶት ብዙ ማሰብና ማጥናት እንዳለበት ገለፀ… ።

ያለ ግን … ግን … አልኩት።

ማስረጃው በጣም ግልጽ ነው። ልትመልሱት አትችሉም። እንደዚሁም በማሳሳቻዎች፣ በመሰለኝና በመላምት እምነታችሁን እያራማዳችሁና ለተዋረደ ጣኦታዊነት ምንም ማስረጃ የለም።

ከዚህያም ከዚህ ማብራሪያና ትንታኔ በኋላ አላህ የቀድሞዎቹን ሙሽሪኮች በሙሽሪክነታቸው የወቀሳቸው እንደ የጉስ፣ የዑቅ፣ ነስር፣ ላት፣ መናት፣ ዑዛና የመሳሰሉትን የሚጠሯቸውን ጣዖታት በመፍጠር ፣ በማስገኘት፣ በማኖር፣ በመግደል፣ በመጉዳትና በመጥቀም ከአላህ ጋር ይጋራሉ ብለው በማመናቸው፣ ወይም በአላህ መኖር በመካዳቸው ወይም የሁሉም ነገር ሥልጣን በአላህ እጅ መሆኑን በማስተባበላቸው ምክንያት አለመሆኑን አንተን ለማሳመን

ከዚህ የበለጠ ንግግሬን ማስረዘም አስፈላጊ አይደለም። ከነዚያ (ከቀድሞዎቹ) ሙሽሪኮች ይህን ያለ (ከአላህ ጋር ይጋራሉ ያለ) ማንም የለምና። አልኩት።

## ሶሻሊስቶች ከኢስላም በፊት

ጓደኛዬ (ተከራካሪዬ) ማስረጃ ያገኘ መስሎት "አዎ" አለ። ቀጠለና "እነዚያ ሙሽሪኮች በአላህ መኖር ይክዱ እንደ ነበር ቁርአን አጽድቆታል። ሙሽሪኮቹ የተናገሩትን አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፦

وَقَالُوا مَا هِيَ إِلَّا حَيَاتُنَا الدُّنْيَا نَمُوتُ وَنَحْيَا وَمَا يُهْلِكُنَا
إِلَّا الدَّهْرُ ۚ وَمَا لَهُم بِذَٰلِكَ مِنْ عِلْمٍ ۖ إِنْ هُمْ إِلَّا يَظُنُّونَ ﴿٢٤﴾

"እርሷም (ሕይወት) የቅርቢቱ ሕይዋታችን እንጂ ሌላ አይደለችም፤ እንሞታለን፤ እንኖራለንም ከጊዜም (ማለፍ) በስተቀር ሌላ አያጠፋንም አሉ፤ ለነርሱም በዚህ (በሚሉት) ምንም እውቀት የላቸውም፤ እነርሱ የሚጠራጠሩ እንጂ ሌላ አይደሉም።" (አልጃሲያ 35:24) አለ።

እነዚህ ቀደም ሲል የተነጋገርንባቸው ሙሽሪኮች አይደሉም። እነዚህ እኮ በጊዜ የሚያምኑ (ዳህርዮች) ከሐዲዎች ናቸዉ። እነሱ እኮ የዛሬዎቹ ሶሻሊስቶች የሚከተሉዋቸዉ ከቀድሞዎቹ

አረቦች አንድ ቡድን (ግንጣይ) ናቸዉ። በአላህ አያምኑም እንደዚሁም ሙሽሪኮች ወደ አላህ ያቃርቡናል በሚሉት ነገር አያምኑም። አላህ አለ የምለዉን ይቃወማሉ። ከዚሁም ጋር

በማያየገ ሙሽሪኮች ወደ አላህ ያቃርቡናል የሚሏቸዉን ታቦታት፣ ጣኦታት የተለያዩ አማልክትም አይቀበሉም። አልኩት።

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የሽርክ መንስኤ በአላህ መኖር ከማመናቸው ጋር ተወሱል ማድረጋቸውና ከአላህ ሌላ ካለው አካል እገዛን መሻታቸው ነው። አላህ እንዲህ ሲል ይጠቅሳቸዋል፡-

وَمَا يُؤْمِنُ أَكْثَرُهُم بِٱللَّهِ إِلَّا وَهُم مُّشْرِكُونَ ﴿١٠٦﴾

"አብዛኞቻቸውም እነሱ አጋሪዎች ሆነው እንጂ በአላህ አያምኑም።" (ዩሱፍ 12:106)

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች በአላህ ባያምኑ ኖሮ ወደ አላህ ያማልዱናል ያሏቸዉን ጣኦታት(አማላጆችን) ባልያዙ ነበር አላህም እንዳለዉ፡-

وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلْفَىٰٓ

" ... እነዚያም ከርሱ ሌላ (ጣኦታትን) ረዳቶች የያዙት ፥ ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም ፥ (ይላሉ) ፡ ... "

(አልዙመር 39:3)

አንተ በማስረጃነት በተጠቀምከው በሱራቱል ጃሲያ ውስጥ አላህን እንደማይቀበሉ የተነገረላቸው ወገኖች ምንነታቸውን የነገርኩህ ሙሽርኮች አለመሆናቸው በዚህ

ይረጋገጣል። እነሱ ደህሪዮች (በጊዜ የሚያምኑ) ዐረቦች ወይም ሹዮዒ (ሶሽሊስቶች) ናቸው። ይህ አገላለጽ ትክክል ከሆነ።

ለያዙት ሽርክ ትክክለኛነት ሲሟገቱ እንኳ "ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንገዛቸውም" (አልዙመር 39:3) እና
"እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው" (የኑስ 10:18) የሚሉ ሰዎች በአላህ መኖር ይክዳሉ ማለት የማይመስል ነው፤ ከወሊዮች አማልክትን የያዙት ወደ አላህ እንዲያቃርቧቸውና እንዲያማልዷቸው እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም። ይህ አንቀጽ የአላህን መኖር በግልጽ መቀበላቸውንና በጌትነቱ አንድነት (በሩቡቢያ) ማመናቸውን ለሚያረጋግጡና ቀደም ሲል ለጠቀስናቸው ሌሎች አንቀጾች ተጨማሪ ነው።

## የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የነበሩበት የሽርክ እውነታ

በውይይቱ የተሰላቸው ጓደኛዬ "እንግዲያውስ እነሱ በዚህ መልኩ በአላህ የሚያምኑና አንድነቱን የሚቀበሉ ከሆነ በቁርአን ውስጥ በአላህ የተወቀሱበትና በሱም ምክንያት ደማቸውና ገንዘባቸው ሐላል የሆነበት ሽርክ የትኛው ነው? በሱ ምክንያት አላህ መልዕክተኛውን እንዲጋደላቸው ያዘዘበት ሽርክ የትኛው ሽርክ ነው?" አለ።
ቁልፍ ጥያቄ ነው። አልኩት።

ይህ ሰዎች መረዳት የሚያቅታቸውና የሚንሸራተቱበት ወሳኝ ነጥብ ነው። ይህን ነጥብ ሰዎች ተገቢውን ትኩረት

በመስጠት ቢያስተነትኑ፣ ቢየስተወሉትና ቢረዱት፣ ተገቢውን ጥናትና ምርምር ቢያደርጉበት አንድ ሙስሊም ነኝ የሚል ሰው ዱዓና ኢስትጋሳን፣ እርድን፣ ነዝርንና የመሳሰሉትን የአላህ መብት ብቻ የሆኑ ዒባዳዎችን ለሌሎች-ለነቢዮችና ለወሊዮች ሲያደርግ አታገኝም ነበር።

## የቀድሞዎቹን የአረብ ሙሽሪኮች ሽርክ በትክክል አለማወቅ የዛሬዎቹን ሰዎች ሽርክ ዉስጥ ከተታቸዉ

ሰዎች ይህንን አደገኛ የሆነዉን ጉዳይ ባለመረዳታቸዉና የቀደሞዎቹ ሙሽሪኮች የነበሩበትን ሽርክ ጠንቅቀዉ ባለማወቃቸዉ ሽርክ ነዉ ብለዉ ሳያስቡ ጭልጥ ያለ ሽርክ ዉስጥ ገቡ፤ (ሙታንን መለመን፣ በነሱም ኢስቲጋሳ ማድረግ፣ አላህ ዘንድ እንድያማልዷቸዉና ወደ አላህ እንድያቃርቧቸዉ ለነሱ ማረድና መሣል) አላህ ከነዚህ ነገሮች አንዱንም ሰይፈቅድላቸው።

## ኢብኑልቀይም ሰዎች ሽርክ ዉስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ መፍራታቸው

ከ13 ምእተ አመት በፊት ዑመር ኢብን አልኸጣብ ሰዎች ዛሬ በገቡበት ሽርክ ዉስጥ ይገባሉ ብሎ መፍራቱን እንዲህ በማለት ገልጧል። "የኢስላም ቋጠሮዎች አንድ በአንድ ይፈታሉ" አለ። (የኢስላም ጥንካሬ ይላላል ማለቱ ነው።) የሙእሚኖች መሪ ሆይ! ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ብሎ ሲጠይቁት "የጃሂሊያን ምንነት የማያውቁ ሰዎች በኢስላም ውስጥ ሲፈጠሩ ነው።" በማለት መለሰለቸው። በዛሬ ጊዜ ከአላህ ጋር ያቃርቡናል ወይም ያገናኙናል በማለት በመተናነስ፣ በመፍራትና በማላቅ ሙታንን የሚጠሩ፣ የሚያርዱላቸውና የሚሳሉላቸው የቅድመ እስላም አረቦች ይህንኑ ያደርጉ እንደነበርና አላህም ይህንኑ ሽርክ ነዉ ኩፍር ነው ብሎ እንደ ገለፀዉ ቢያዉቁ ኖሮ ባልተገበሩትና ባላመኑበትም ነበር። ይህ ድርጊት ሲተችና ሲወገዝም ባልተቆጡና ባልደነፉም ነበር።

እንዳብራራልህና ግልጽ እንዳደርግልህ የጠየከኝ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የሽርክ አይነት፡- የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች በአላህ መኖር ከማመናቸውና ያለ ምንም አጋር የፍጥረተ ዓለሙን ሁኔታ እንደሚያስተናብር ከመቀበላቸው ጋር አላህ ያለዘዘውን አዲስ ፈሊጥ (ቢድዓ) አመጡ። ይህን ያመጡትን ቢድዓ ወደዱት፤ ናፍሳቸውም ተረጋግታ ተቀበለችው። እሱም ከፍጥረታት እንደላት፣ ዑዛ፣ መናት፣ የጉስ፣ የዑቅና ነስር የተባሉትን ፍጡራን ወሊዮችና አገናኞች ናቸው ብለው ማመናቸው፣ ወደነሱም መጠጋታቸው፣ ወደ አላህ እንዲያቃርቧቸውና ጉዳያቸው እንዲፈፀምና ከጭንቀትም ለመውጣት አላህን ያማልዱናል በማለት በዱዓእ፣ በነዝር (ስለት)ና በእርድ ወደነሱ መቃረባቸው ነው። ይህን ደግሞ አላህ ሳይፈቀድላቸውም ሳይወድላቸውምም ነው!!

ይህ ደግሞ አላህ በቁርአኑ እነሱን የወቀሰበትና ያወገዘበት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ
مَا لَا يَضُرُّهُمۡ وَلَا يَنفَعُهُمۡ وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا
عِندَ ٱللَّهِۚ قُلۡ أَتُنَبِّـُٔونَ ٱللَّهَ بِمَا لَا يَعۡلَمُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا
فِي ٱلۡأَرۡضِۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿١٨﴾

"ከአላህ ሌላ የማይጐዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይገዛሉ፤ እነዚህም አላህ ዘንድ አማለጆቻችን ናቸው ይላሉ፤ አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን? በላቸው፤ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፤ ላቀም።" (ዩኑስ 10:18)

ይገዛሉ ማለት ይጠራሉ(ይለምናሉ) ማለት ነዉ። እንደዚሁም ደግሞ አላህ እንዲህ ይላል:-

مَا لَكُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَلِيّٖ وَلَا شَفِيعٍۚ أَفَلَا تَتَذَكَّرُونَ ﴿٤﴾

"ከርሱ ሌላ ለናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም፤ አትገሰጹምን?" (አልሰጅዳ 32:4)

## ወሊዮችን ወደ አላህ አማላጅ አድርጎ መያዝ ራሱ ኩፍር መሆኑ

በዚህ ፍልስፍና መሠረት ማለትም ወሊዮች ናቸው በተባሉት በነዚህ አማልክት ተወሱል (መቃረብ)፤ እና ተሸፍፋዕ (መማለድ) ይቻላል በሚለው ፍልስፍና መሠረት ይጠሯቸው፣ እርዳታን ይለምኗቸው፣ ያርዱላቸውና ይሳሉላቸው

ነበር፡፡ የመመለሽ ጣቢያቸው ፣ የመጨረሻ ተስፋቸውና ወደ አላህ መዳረሻ በራቸው በማድረግም በሐውልቶቻቸው ዙሪያ ይዞሩ (ይጠውፉ) ነበር፡፡

ይህንንና የመሣሰሉትን ነዉ አላህ ያወገዘዉና ሽርክ ነዉ ኩፍር ነዉ ብሎ ደማቸዉንና ገንዘባቸዉን የፈቀደዉ፣ ለዚሁ ነዉ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) በበድር፣ በኡሑድ፣ በኸንደቅ በሑነይንና በሌሎችም በሰይፍ የተጋደሏቸው፡፡

ለዚሁ ነዉ በነቢዩና ዘመዶቻቸዉ መሃል የነበረዉ ዝምድና የተቆራረጠዉ፡፡

አላህ ይህንኑ ነበር ከኔ ውጭ ላለ ነገር ዒባዳ አደረጉ፣ በኔም አጋሩ፣ ብሎ የገለፀው፤ ለዚሁ ነበር የተቆጣባቸውና ከረሀመቱም ያራቃቸው፡፡ ምክንያቱም እነሱ ይህንን መንገድ ስለተከተሉና ይህንን ቢድዓ ስለፈጠሩ ነው፡፡ አገናኞችን (ውሰጣእ) እና አማላጆችን (ሹፈዓእ) የመያዝ ቢድዓ ፈጥረው ወደ አላህ መዳረሻ በር እንዲሆኑላቸው በነሱ ላይ በመመካታቸውና ወደነሱም በመጠጋታቸው ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذْنِهِۦ

"... እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማን ነው? ... " (አልበቀራ 2:255)

ጓደኛዬ፡ "ይህም ቢሆን ጠቅለል ያለ ንግግር (አገላለጽ) ነው፤ ትክክለኛነቱን የሚገልጽ ቁርጥ ያለ አሳማኝ? ማስረጃ

የለበትም፣ ለትክክለኛነቱ ማረጋገጫ ዘርዘር ያለ መስረጃ ምንድ ነው?" አለኝ።

አሁንም ማስረጃው ያለው በአላህ ኪታብ (ቁርአን) ውስጥ ነው። አልኩትና የሚከተለውን የአላህ ቃል አነበብኩለት።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَٱسْتَمِعُوا۟ لَهُۥٓ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ
تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَن يَخْلُقُوا۟ ذُبَابًا وَلَوِ ٱجْتَمَعُوا۟ لَهُۥ ۖ
وَإِن يَسْلُبْهُمُ ٱلذُّبَابُ شَيْـًٔا لَّا يَسْتَنقِذُوهُ مِنْهُ ۚ ضَعُفَ
ٱلطَّالِبُ وَٱلْمَطْلُوبُ ﴿٧٣﴾ مَا قَدَرُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦٓ ۗ إِنَّ
ٱللَّهَ لَقَوِىٌّ عَزِيزٌ ﴿٧٤﴾

"እናንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተደርጐላችኋልና አድምጡት፣ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸው (የሚትገዟቸው ጣዖታት) ዝንብን ፍጽሞ አይፈጥሩም፣ ለርሱ (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳ (አይችሉም)፣ አንዳችም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከርሱ አያስጥሉትም፣ ፈላጊውም ተፈላጊውም ደከሙ። (ገዢም ተገዢውም ደካሞች ናቸው።) አላህን ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም፣ አላህ በጣም ሐያል አሸናፊ ነው።" (አል-ሐጅ 22:73-74)

ቀደም ሲል በተጠቀሰዉ በዩኑስ ምዕራፍም ከሱ ሌላ መጥራታቸዉንና እሱ ዘንድ የሚያማልዱዋቸዉን አማላጆችን መያዛቸዉን አውግዟል። እንደዚሁም ይህ ተግባር በሱ ማሻረክና ከሱ ሌላ ያለዉን ማምለክ እንደሆነ እንዲህ በማለት ገልፆታል፦

وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمۡ وَلَا يَنفَعُهُمۡ
وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا عِندَ ٱللَّهِۚ

"ከአላህም ሌላ የማይጐዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይገዛሉ፣ እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ ፤ ..."

ከዚያም ቀጠለና ይህ አባባላቸው ከንቱ መሆኑን በመግለጽና የምልጃና የተወሱል ጽንሰ-ሐሳብ ውድቅ መሆኑን በመናገር በቁጣ መልክ እንዲህ አለ፡-

قُلۡ أَتُنَبِّـُٔونَ ٱللَّهَ بِمَا لَا يَعۡلَمُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا
فِي ٱلۡأَرۡضِۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ١٨

"አላህን በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን? በላቸው ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ ላቀም።" (ዩኑስ 19:18)

አላህ (ሱ.ወ) ስለባሪያው ሁኔታ የማያውቀው ነገር ስለሌለና ከሱ የተሰወረ ነገር ኖሮ አማላጆች ሊናገሩት የሚያስፈልገው ነገር ስለሌላ አንድም ሰው በዚች ዓለም በአማላጅ ወይም በአገናኝ ወደሱ እንድቀርብ አይፈልግም። አላህ ከዚህ አይነቱ እንከን የጠራ ነው።

ከሷሊሆች ውስጥ መልካምና ጻድቃን ናቸው ብለው በሚገምቱዋቸው ሰዎች ወደ አላህ መማለዳቸውን ሲያወግዝና

እነዚህ እነሱ ከሱ ሌላ የሚጠሯቸው ሰዎች እንኳንስ ከነሱ ጉዳትን መከላከል ወይም ከፉን ነገር መመለስ ቀርቶ፣ ለራሳቸውም መልካሙን ነገር ማምጣት ወይም ከራሳቸው ጉዳትን መከላከል የማይችሉ ልክ የነሱ ብጤ ባሮች መሆናቸውን፣ እንዲያውም ወደ አላህ ከመቅረባቸውም ጋር ለራሳቸውም ቢሆን ወደሱ የሚቃረቡት እርሱን በመፍራት ከረህመቱም በመከጀል መሆኑን ሲገልጽ አላህ እንዲህ ይላል፡-

قُلِ ادْعُوا الَّذِينَ زَعَمْتُم مِّن دُونِهِۦ فَلَا
يَمْلِكُونَ كَشْفَ الضُّرِّ عَنكُمْ وَلَا تَحْوِيلًا ﴿٥٦﴾ أُولَٰٓئِكَ الَّذِينَ
يَدْعُونَ يَبْتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ الْوَسِيلَةَ أَيُّهُمْ أَقْرَبُ وَيَرْجُونَ
رَحْمَتَهُۥ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُۥٓ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحْذُورًا ﴿٥٧﴾

"እነዚያን ከርሱ ሌላ (አማልክት) የምትሏቸውን ጥሩ፤ ከናንተ ላይ ጉዳትን ማስወገድም ሆነ (ወደ ሌላ) ማዞር አይችሉም በላቸው። እነዚያ እነርሱ የሚጠራቸውማንኛ ቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃ ረቢያ (ሥራ) ይፈልጋሉ ፤ እዝነቱንም ይከጅላሉ ፤ ቅጣቱን ይፈራሉ ፤ የጌታህ ቅጣት የሚፈራነውና።"

(አል-ኢስራእ) 17:56-57)

ከርሱ ሌላ ፍጡራንን መጥራት ሽርክ መሆኑን ሲገልጽ አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَٱلَّذِينَ
تَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ مَا يَمۡلِكُونَ مِن قِطۡمِيرٍ ﴿١٣﴾ إِن
تَدۡعُوهُمۡ لَا يَسۡمَعُواْ دُعَآءَكُمۡ وَلَوۡ سَمِعُواْ مَا ٱسۡتَجَابُواْ لَكُمۡۖ
وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَكۡفُرُونَ بِشِرۡكِكُمۡۚ وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثۡلُ خَبِيرٍ

"... እነዚያም ከርሱ ሌላ የምትጠሯቸው የተምር ፍሬ ሽፋን እንኳ አይኖራቸውም። ብትጠሯቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም፤ ቢሰሙም ኖሮ ለናንተ አይመልሱላችሁም፤ በትንሳኤም ቀን (እነርሱን በአላህ) ማጋራታችሁን ይክዳሉ፤ እንደ ውስጠ አዋቂው ማንም አይነግርህም።" (ፋጢር 35:13-14)

لَهُۥ دَعۡوَةُ ٱلۡحَقِّۖ وَٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ لَا يَسۡتَجِيبُونَ لَهُم بِشَيۡءٍ إِلَّا
كَبَٰسِطِ كَفَّيۡهِ إِلَى ٱلۡمَآءِ لِيَبۡلُغَ فَاهُ وَمَا هُوَ بِبَٰلِغِهِۦۚ وَمَا دُعَآءُ ٱلۡكَٰفِرِينَ
إِلَّا فِي ضَلَٰلٍ ﴿١٤﴾

"ለርሱ (ለአላህ) የእውነት መጥሪያ አለው (በእውነት የሚጠራው እርሱ ብቻ ነው)፤ እነዚያም ከርሱ ሌላ የሚጠሯቸው (ጣዖታት) ወደ አፉ ይደርስ ዘንድ ወደ ውሃ መዳፎቹን (በሩቅ ሆኖ) እንደሚዘረጋ (ሰው መልስ) እንጂ ለነርሱ በምንም አይመልሱላቸውም፤ እሱም ወደ አፉ ደራሽ አይደለም፤ የከሐዲዎችም ጥሪ በከንቱ እንጂ አይደለም" (አል-ረዕድ 13:14)

أَلَا لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلْخَالِصُ ۚ وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلْفَىٰٓ إِنَّ ٱللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِى مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى مَنْ هُوَ كَٰذِبٌ كَفَّارٌ ﴿٣﴾

"ንቁ፤ ፍጹም ጥሩ የሆነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው። እነዚያም ከርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች አድርጉ የያዙት ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንገዛቸውም (ይላሉ)፤ አላህ በዚያ እነርሱ በርሱ የሚለያዩበት ነገር በመካከላቸውም ይፈርዳል፤ አላህ እርሱ ውሸታም ከሐዲ የሆነን ሰው አያቀናም።" (አልዙመር 39:3)

እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ የተጠቀሱት ማስረጃዎች የነገርኩህን የሙሽሪኮቹን ሁኔታ ትክክለኛነት ያረጋግጡልሃል፤ የነበሩበትን የሽርክ እውነታም ያብራሩልሃል። ብዙ ሰዎች ምንነቱን ባለማወቅ የሚገቡበት ሽርክም ይኸው ነው።

## የቁቡሪዮች ትልቁ ማሳሳቻ ማምከን

ጓደኛዬ: "እነዚህ የጠቀስካቸው አንቀጾች በቅድመ ኢስላም (በጃሂሊያ) ለነበሩ የዐረብ ሙሽሪኮች የወረዱና ለነሱ ብቻ የሚጠቀሱ እንጂ በዛሬ ጊዜ በወሊዮች ኢስትጋሳ ከሚያደርጉት ሰዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም። በነሱ ላይ በማስረጃነት ሊጠቀሱም አይችሉም።" አለኝ።

ይህቺማ የተጋለጠች ማሳሰቻና ፉርሽ የሆነች ማስረጃ (መከራከሪያ) ነች። አልኩት።

በርግጥ እነዚህ እናቅጽ የወረዱት በዐረብ ሙሽሪኮች ዘመንና እነሱን በማስመልከትም ነበር። ሙሉው ቁርአንም የወረደው በዚያው ዘመን ነበር። ግን ይህ ዘውታሪ የሆነው መጽሐፍ (ቁርአን) በሁሉም ዘመንና ቦታ ላሉ ባሮቹ አላህ ያስተላለፈው መልዕክት ነው። ትእዛዛቱ ዘውታሪ ስለሆኑ መፈፀማቸው ግዴታ ነው። በቁርአን የተከለከሉት ነገሮችም እንደዚሁ ለሁልጊዜ ስለሆኑ ከነሱ መራቁ እስከ አለተ ትንሳኤ ድረስ ግዴታ ነው።

የቁርአን መልእክት ወይም ቃል አጠቃላይ እንጂ በአንድ በተወሰነ ምክንያት የተገደበ አይደለም። የአንድ ነገር ፍርድ የሚሄደው ከምክንያቱ ጋር መሆኑን በየተኛውም ቦታና ጊዜ ምክንያቱ ጋር መሆኑና በየትኛውም ቦታና ጊዜ ምክንያቱ ከተገኘ ያ ፍርድ ተፈፃሚ መሆኑ በሁሉም ሙስሊሞች ዘንድ የሚታመንና የፀና ሕግ ወይም መርህ ነው።

የቀድሞዎቹን ሙሽሪኮች ሽርክ አስመልክቶ ይህ የተባለው ምንክያት እነሱ ዘንድ አማለጆች እንዲ ሆኑላቸው በነሱ ላይ መመካታቸው ነበር። ይህ ደግሞ የዛሬዎቹ ቁቡሪዮች እየፈፀሙት ያሉ ነው፡- ወሊዮችን መጥራት ፣ ወደ አላህ ዋሲጣ (አገናኝ) እንዲሆኑላቸው በነሱ ኢስቲጋሳ ማድረግ። በዚህ የተነሳ ነው ያለምንም ልዩነት በሁለቱም (የቀድሞቹና ባሁኖቹ) ላይ የሽርክ ሑክም (ፍርድ) የሚሰጠው። ምክንያቱም በዓላማም ሆነ በተግባር አንድ ሆነዋልና። እሱም በአላህ ዘንድ አማላጅ እንዲሆንላቸው

በማለት በዱዓእ፣ በእርድና በስለት ከአላህ ሌላ ወደ ሆነ ነገር መዞር ነው።

"በዚህ ንጽጽርሽህ (ቂያስህ) መሠረት አንዱን ከሌላው ሳትለይ በሁለቱም ወገን ላይ የሽርክ ሑክም (ፍርድ) መስጠትህ ተገቢ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ንጽጽርሽ ነው። የማይገናኝ ነገር አገናኘተሃል።" አለኝ።

አሁን ብዙ ደክሜ የቀድሞዎቹን ሙሽሪኮች ካፊር ያደረጋቸዉ አማላጆችና አገናኞች መያዛቸዉና ወደነሱም በዱአእ፣ በስለትና በእርድ መቃረባቸዉ መሆኑን ግልጽ አድርጌልሃለዉ። የዛሬዎቹ የመቃብር አምላኪዎች ይህንኑ መንገድ ሙሉ በሙሉ ስንዝር በስንዝር እንደሚከተሉ አብራርቼልሃለዉ፤ አንተ ደግሞ ሁለቱም በሐሳብና በተግባር አንድ ከመሆናቸዉ ጋር የነዚያ ስራ ኩፍርና ሽርክ ሆኖ አላህ እስከ ዘልዓለሙ በእሣት የሚቀጣበትና የነዚህን ደግሞ አላህ የሚወደውና የሚፈቅድ ተወሱልና ቅጣት የሌለበት የሚያደርገዉ ምንድን ነዉ? ያለዉን ልዩነት ብታብራራልኝ? አልኩት።

"ልዩነታቸዉ በብዙ መልኩ ነዉ።" አለ።

"አንደኛ:- የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ከአላህ ሌላ ይገዛሉ። ይህንንም ማድረጋቸዉን አምነዉ መቀበላቸዉን ቁርአን እንዲህ ሲል ያረጋግጣል:-

مَا نَعۡبُدُهُمۡ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلۡفَىٰٓ

"ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም (ይላሉ) ፡"

በወሊዮች ተወሱል የሚያደርጉት የዛሬዎቹ ሰዎች ግን ከአላህ ሌላ መገዘትን ይፃረራሉ። "እኛ ሙታን ወሊዮችን ስንጠራ (ስንለምን) በነሱ ስንመጀን እነሱን ማምለክን አስበን (ነይተን) ሳይሆን ተወሱልና ተበሩክ ፈልገን ነዉ" ይላሉ። "እዚህ ላይ ነው በሁለቱ መሀል ያለው ልዩነት።" አለኝ።

## የቃላት መለዋወጥ የአንድን ነገር እዉነታ አይቀይረዉም

ቀደም ሲል እንዳልኩህ ፍርድ(ሑክም) የሚሰጠዉ ሐሣብና ተግባር ላይ በመመርኮዝ ስለሆነ አንድ ሰዉ ከራሱ ለመከላከል ለሚጠቀምባቸዉ ቃላቶች ቦታ አይሰጣቸዉም የአንድ ፍርድ መንስኤ ተግባሩ እስከሆነ ድረስ።

ለምሳሌ አንድ ሰዉ ለጣኦት ሁል ጊዜ ሱጅድ ቢያደርግና፣ ከአላህ ሌላ መገዛትን ደግሞ እንደሚቃወም በአፉ ቢናገር፣ ከአላህ ሌላ አላመለክሁም፣ አላመልክምም ብል ይህ አባባሉ ከዚህ ድርጊቱ ጋር ሙሽሪክ ነዉ ከመባልና የኩፍር ሑክም በሱ ላይ ከማሰጠት ያድነዋል ወይ? አልኩት።

"እንዴታ... እሱማ ካፊር ሙሽሪክ ነዉ" አለኝ።

እንግዲያውስ በዛሬዎቹ ቁቡሪዮች ላይም ሊሰጥ የሚገባና ሙሉ በሙሉ ተስማሚ የሆነ ፍርድ ነው። ተግባራቸዉ ከሙሽሪኮች ጉራ አስፈርጀዋቸዋል። ከመሆኑም ጋር ይህንን አይቀበሉም ይክዳሉ።

በነሱና በቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች መሃከል ያለዉ ልዩነት የቀድሞዎቹ ከአላህ ሌላ ማምለካቸዉን ሲያምኑ በጣም ግልጽ መሆናቸዉ ሲሆን፣ የአሁኖቹ የመቃብር አምላኪዎች ደግሞ በጣም ድብቆችና አሣሣቾች መሆናቸዉ ነዉ። ከአላህ ሌላ እያመለኩ አላመለክንም ብለዉ መካዳቸዉና ለድርጊታቸዉ ሌላ ስም መስጠታቸዉ ነው። አልኩት።

ለማሣሣት እየሞከረ "እኔ ቀደም ሲልም እንዳልኩህና ምንጊዜም እንደምለው የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ስራ ከአላህ ሌላ መገዛት ስለ ሆነ ሙሽሪኮች፣ ኩፋሮች ለማባል በቅቷል።"

"ነገር ግን የዛሬዎቹ በወሊዮች የሚመጃኑትና በነሱ ተወሱል የሚያደርጉት ወሊዮችን መገዛታቸዉ ስላልሆነ ሙሽሪኮችና ኩፋሮች መባል አይገባቸዉም።" አለኝ።

ሐቅን ከመቀበል ለመሸሽ በሚታደርገው ተደጋጋሚ ሙከራዎች ብዙ አድክመሀኛል፤ እኔ ግን እንዳንተ አይነት ሕሊና ያለው ሰው ሐቅን ላለመቀበል እንደዚህ ይሆናል ብዬ አልገመትኩም ነበር።

የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች በአላህ መኖር የማመናቸዉን እውነታ የጌትነቱን አሐድነት(ተዉሂድ አል-ሩቡቢያን) ሙሉ በሙሉ መቀበላቸዉን፣ የነበሩበት ሽርክ ምን እንደነበረና ሙሽርክ ለመሰኘት ዋነኛዉ ምክንያት ምን እንደሆነ ተጨማሪ ማብራሪያ በማያሻዉ መልኩ አብራርቼልሃለዉ።

እንደዚሁም የሙታን አምላኪዎችን ሙሽሪኮች ብለን መጥራታችን ዝም ብሎ ሳይሆን ድርጊታቸውን ከቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች እነዚያ ቁርአን ከአንድ ሺህ ሃስት መቶ አመት በፊት ሙሽሪኮች ብሎ ከወሰነባቸዉ ድርጊት ጋር በማነፃፀር እንደሆነ ዘርዝሬልሃለዉ። በትክክለኛ ንጽጽሮሽና ጥልቀት ባለዉ ምርመራ የዛሬዎቹ የሙታን አምላኪዎች ለወሊዮቻቸዉ የሚያደርጉት ስለት፣ የሚያቀርቡት እርድ፣ እነሱን መለመን በነሱ መመጀን፣ እነሱን መፍራትና እነሱን መከጀል ከአላህ ሌላ ያለዉን ማምለክ እንደሆነ ደርሰንበታል።

ምክንያቱም ይህ ድርጊታቸው በትክክል የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ለወሊዮቻቸዉ ያደርጉት የነበረዉና አላህም ከሱ ሌላ መገዛት እንደሆነ ያፀደቀዉ በመሆኑ ነዉ። ነገር ግን አንተ ችክ ብለህ በሁለቱ መሃል የሁክም (ፍርድ) ልዩነት አለ ብለህ ትከራከራለህ። ሁለቱም በዓላማና በተግባር አንድ ከመሆናቸውና ከአላህ ሌላ መገዛታቸው አንድ የሚያደርጋቸው ከመሆኑም ጋር እንዲህ ትከራከራለህ።

ይህ አመለካከትህ እስከሆነ ድረስ ዘርዘር አድርገህ እንድትመልስልኝ እምፈልገው አንድ ጥያቄ አለኝ። እሱም፦

ሙሽሪኮች ከአላህ ሌላ ያመለኩትና አላህም በሱ ምክንያት ሙሽሪኮች ብሎ የጠራቸውና ኩፍርን የወሰነባቸዉ የአምልኮ አይነት ምን እንደሆነ ልታብራራልኝ ትችላለህ?

ከአላህ ሌላ ያለዉን መጥራት፣ ከሱ ውጭ ላለዉ መሣልና ማረድ ትልቁ ሽርክ ነዉ።

"ለዚህ ጥያቄዬ መልስ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም በሁለቱ መካከል ልዩነት ካለ፣ ያለውን የሁለቱን ልዩነት መረዳት እንድንችልና የአንተን አመለካከት ትክክለኛነት እንድነውቅ ነው። የቀድሞዎቹን ሙሽርኮች ድርጊት ከአላህ ሌላ ማምለክ ነው ብለህ ፍርድ የሰጠህበትና የአሁኖቹን ቁቡሪዮች ከዚህ ፍርድ ነፃ ያደረከበትን የአመለካከትህን ተክክለኛነት እንደነውቅ መልሱን ስጠኝ።" አልኩት።

እዚህ ላይ ግራ ተጋባ። ጥያቄው ጆርባውን የሚለበልብ ጅራፍ መሰለው። ጥያቄው በሁለቱ የወፍጮ ድንጋዮች መሃል አስገባው። ነገር ግን እጅ አልሰጠም። ይሁን እንጂ እጅግ ግራ ከመጋበቱ የተነሳ በውይይታችን ወቅት ላለመቀበል ሲሸሽ የነበረውን እውነታ ተቀበለ።

እንዲህ አለ:- "በርግጥም መቀበሉ ግዴታ የሚሆን እውነታ አለ፤ እሱም የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ጣዖቶቻቸው እንደማይፈጥሩ፣ እንደማይረዝቁ፣ ሕያው እነደማያረጉ፣ እንደማይገድሉ፣ ክፉን ነገር እንደማይመልሱና መልካም ነገር እንደማያስገኙ ከማወቃቸው ጋር በዱዓእ፣ በእርድ፣ በስለት፣ በጠዋፍና በመሳሰሉት የአምልኮና የመቃረቢያ አይነቶች ወደነሱ ከመቃረብ ባሻገር ለጣዖቶቻቸው የሚያደርጉት ነገር ያለመኖሩ ነው።"

"ይህን ሲያደረጉላቸው ትልቁ ዓላማቸዉ ጣኦታት ስራቸዉን ወደውላቸው ወደ አላህ እንድያቃርቡዋቸዉና አላህ ዘንድ አማላጅ ሆነዉላቸዉ የአላህን እዝነት (ራህመት)ና ጥበቃዉን እንድያስገኙላቸዉ ነዉ።"

"አላህ ሙሽሪኮች ብሎ የጠራቸዉና የኩፍርን ሑክም የሰጣቸዉ የማልክድህና በግልጽ የምናገረዉ ከአላህ ሌላ የማምለካቸው እዉነታ ይህ ነዉ።"

"የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የነበሩበት የሽርክ እውነታ ይህ መሆኑን አላዉቅም ነበር፤ ይህንን የተረዳሁት አሁን ካደረግነዉ ውይይት ነዉ።" አለ።

ትልቅ ነገር ነዉ! ከዚህ ሁሉ ክርክር በኋላ በአንድ ዋነኛ ነጥብ ላይ ተስማምተናል ማለት ነዉ። እሱም የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የነበሩበት አምልኮ ምን እደነበር መወሰን ነው። ይህ ማለት ደግሞ ዱአእ፣ እርድ፣ ጠዋፍ፣ ስለት፣ መዋረድና መተናነስ አምልኮ መሆኑን ትቀበላለህ ማለት ነዉ። አልኩት።

## በዛሬዎቹ ቁቡርዮችና በቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች መካከል ምንም ልዩነት የለም

ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሰጥተሃል። አሁን ደግሞ ሌላ ጥያቄ አለኝ። ልክ የመጀመሪያውን በመልስክልኝ መልኩ ይህንንም ግልጽነት በተሞላበት ሁኔታ እንድትመልስልኝ እፈልጋለሁ።

የዛረዎቹ ቁቡሪዮች ሙታን ወሊዮቻቸዉን ስራቸዉን እንዲወዱላቸዉና አላህ ዘንድ እንድያማልዱዋቸዉና ሽፋአ እንድያስገኙላቸዉ በዱአእ፣ በእርድ፣ በስለት፣ በመተናነስና በፍርሃት ይማፀኑዋቸው የለም ወይ? አልኩት።

"ይህማ በጭራሽ ሊካድ የማይችል ተጨባጭ ባህሪያቸው ነው።" አለ።

እንግዲያውስ በዚህ ረገድ ሁለቱም ወገን እኩል መሆናቸዉን ተማመን ማለት ነዉ። ቁቡርዮች በዱአእ፣ በመተናነስ፣ በእርድና በጠዋፍ ወሊዮቻቸዉን እንደሚማፀኑ ሁሉ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ደግሞ ከአላህ ሌላ ለሚያመልኳቸዉ ጣኦታት ያደርጋሉ። ይህም ማለት ደግሞ ሁለቱም ወገን በአምልኮ ከአላህ ሌላ ወዳለዉ ይሄዳሉ (ይዞራሉ) ማለት ነዉ። ይህ ነዉ እንግዲህ አላህ ሐራም ያደረገዉ ሽርክ።

"በአላማ፣ በሐሣብና በተግባር ከቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ጋር እኩል የሆኑት እነዚህ ቁቡርዮች በዚህ ድርጊታቸዉ በአላህ እንዳሻረኩ አምነህ ለመቀበል የሚያግድህ ነገር ይኖራልን? አልኩት።

## ጣኦታትን በመጥራትና ወልዮችንና ሷሊሆችን በመጥራት መካከል ልዩነት ይኖራልን?

"አዎን፣ ይህንን ለመቀበል የሚያገደኝ አለ። እሱም የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች የሚጠሯቸው በእጃቸዉ

የሰሩዋቸውንና አላህ ዘንድ ምንም ክብርና ቦታ የሌላቸውን ሲሆን ቁቡርዮች (በናንተ አጠራር) ግን የሚጠሩአቸውና የሚመጀኑባቸው አላህ ዘንድ ክብርና ቦታ ያሉዋቸዉን ወልዮችና ሷሊሆችን ነው። አላህም እንዲህ ብሎዋል፡-

أَلَآ إِنَّ أَوْلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ

"ንቁ! የአላህ ወዳጆች በነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም ፤ እነሱም አያዝኑም።" (ዩኑስ 10:62)

"ሙሽሪኮች አማልክት አድርገው በመያዝ በሚያመልኳቸው ድንጋዮችና ታቦታት መካከልና ጠሪዎቻቸው ከአላህ ሌላ አማልክት ናቸው ባሉዋቸው ወሊዮችና ሳሊሆች መካከል ያለው ልዩነት ትልቅ ነው።" አለ።

ወደ ሐቅና ትክክለኛዉ መንገድ የሚያደርሰዉን ጉዳና ይዘሐል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር። ነገር ግን አንተ በጣም በሚያሣዝን ሁኔታ ተመልሰህ ታጥቦ ጭቃ ሆነሃል። የማምታቻ መንገድ በመከተል ውይይታችንን ከንቱና ዞሮ እዚያው አድርገሀዋል።

ይህ አንተ ያደረከዉ ክፍፍል በጣም ሞኝነትና ጅልነት የተሞላበት ነዉ። የማሳመኛ ነጥብህ ከድክመት የመነጨና እንኳንስ ለመቀበል ቀርቶ ለማስማትም የሚየስጠላ ነው።

በመላዉ ሙስሊም ህብረተሰብ ዘንድ የሚታወቀዉና እንደ መርህ የሚታየው በማንኛውም የአምልኮ አይነት

ከአላህ ሌላ ወዳለው ነገር መዞር (አምልኮን ለሌላ ማድረግ) በአላህ መካድና ከኢስላም የሚያስወጣ ሽርክ መሆኑ ነው።

በዚህ ረገድ አምልኮው የሚደረግለት ነገር፣ የተላከ ነቢይም ይሁን፣ ወደ አላህ ቅርበት ያለው መልአክም ይሁን፣ ቅዱስ የሆነ ወሊይም ይሁን፣ ምንም የማይሰማ ድንጋይም ይሁን፣ አመፀኛው ሸይጣንም ይሁን ሁሉም እኩል ናቸው። ምንም ልዩነት የላቸውም። በዚህ ነጥብ ላይ ሁለት ሙስሊሞች እንኳ አይለያዩበትም። ዱአእ፣ እርድ፣ ስለትና፣ ጠዋፍ አምልኮ መሆናቸዉን በዚህ ውይይታችን ውስጥ አምነህ ነበር።

ሙሽሪኮች ለጣኦታቸዉ የሚያደርጉትን የአምልኮ ተግባራት ሽርክና ኩፍር ነዉ ማለትህና ያሁኖቹ የሙታን አምላኪዎች በዚሁ መልኩ ለወሊዮቻቸው የሚያደርጉትን አምልኮ፣ አምልኮ አይደለም፣ ሽርክም አይደለም፣ ማለትህ እውነትን ከመቀበል መዞርና እንደ ፀሐይና ጨረቃ ቁልጭ ብሎ የሚታየውን እውነታ ለመካድ መሞከር ነው።

ይህ አንተ ያደረከዉ ክፍፍል ከቁርአንም ሆነ ከሐዲስ የሚደግፈው ማስረጃ የለዉም። የሰዉ አእምሮም የሚቀበለዉ አይደለም። ባይሆን ይህንን የምትናገረው የእምብተኝነትና የኩራት መንፈስ ተጠናዉቶህ ነዉ። ይህን ሁሉ ውይይት ካደረግን በኋላ የእምቢተኝነትና የኩራት ምርኮኛና መስዋዕት የምትሆን አይመስለኝም ነበር። አልኩት።

"እኔ የእምቢተኝነት ምርኮኛና የኩራት ተገዢ አይደለሁም፤ ነገር ግን እኔም እንዳንተው የማምንበትንና

የመሰለኝን የመግለጽ መብት ያለኝ ሰዉ ነኝ። ይህ ደግሞ እስከ መቼዉም የማምንበት ጉዳይ ነዉ። እንደዚሁም ደግሞ በውይይታችን ላይ ግልጽ እንድንሆንና የግል ስሜታችንን ወደ ጐን እንድንተው በውይይታችን መግቢያ ላይ የተስማማንበት ጉዳይ ስለሆነ ስሜታዊ እንዳትሆንና የመሰለኝን ሁሉ የመግለጽ መብቴን ብትተውልኝ ደስ ይለኛል።

እኔ የምልህ ካልተዋጠልህ የማፍረስና በምታምንበት ማስረጃ አስደግፈህ ያለመቀበል መብትህ የተጠበቀ ነዉ። ይህ ደግሞ መሆን ያለበት ያለምንም ድንፋታና ቀለል ባለ አገላለጽ ነዉ። ምክንያቱም ድንፋታና መጥፎ አገላለጽ በውይይታችን ላይ አሉታዊ ተጽኖ ስለሚኖረውና ይህን ሁሉ ውይይት ክርክር ያደረግንበትን አላማ ዉጤት አልባ ስለሚያደርገዉ ነዉ።" አለ።

እኔም በውይይት ወቅት ስሜታዊነትና ድርቅ ያለ አገላለጽ ለዉጤት የማያበቁ በመሆናቸዉ ላይ እኔም ካንተ ጋር ነኝ። በተቻለኝ መጠን ጥሞት ነው ከምለው ነገር ውስጥ ላወጣሀ ከልብ እጥራለሁ። አልኩት።

## የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ሽርክ ወሊዮችንና ሷሊሆችን በማምለካቸዉ እንጂ በሌላ አልነበረም።

ምንም እንኳን አንተ የሁለቱ ወገኖች ሑክም የተለያየ ነው ማለትህን ብትገፋበትም፣ ማስረጃህ (በትክክለኛዉ አገላለጽ ማሣሣቻህ) የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ጣዖቶቻቸውን ከድንጋይ ቀርጸዉ ወደ አላህ ያቃርቡናል ማለታቸውና፣

የዛሬዎቹ የሙታን አምላኪዎች ደግሞ በአማላጅነት የሚጠሯቸው ወሊዮችንና ሷሊሆችን ነዉ የሚለዉ ነዉ። እኔ ግን ይህንን ደካማ ማሣሣቻህን በበቂ ማስረጃ ውድቅ አድርጌ፣ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች እንደ ዛሬዎቹ ቁቡሪዮች መሆናቸዉን ላረጋግጥልህ እችላለሁ። እነሱኮ የሚያርዱላቸው፣ የሚሳሉላቸው፣ የሚጠውፉአቸው፣ የሚጠሯቸውና የመሳሰሉትን የአምልኮ ተግባራትን የሚያደርጉላቸው መልካምና ቅዱሳን ናቸው ብለው ለሚያምኑባቸው ከሰው ልጆች ለሆኑ የአላህ ባሮች እንጂ ለሌላ አይደለም። እውነታው ከታየ እነሱ ይገዟቸው የነበሩት ወሊዮችንና ሳሊሆችን እንጂ ሌላ አልነበረም።

ጣኦታትንና ታቦቶችን ራሳቸውን ሳይሆን የሚያመልኩት እነሱን የሚወክሉዋቸዉን እንደ (የጉስ፣ የዑቅ፣ ወድ፣ ነስር፣ ሱዋዕ፣ ላትና ዑዛ) የመሣሠሉትን ነዉ።

የቀደሞዎቹ ሙሽሪኮች እንደ ዛሬዎቹ ቁቡርዮች ወሊዮችንና ሷሊሆችን ይገዙና ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ይይዟቸው እንደነበር ማስረጃው ያለው ቁርአን ውስጥ ነው። እናንተ ግን አትመሩበትም። አላህ እንዲህ በማለት ገልፆዋል፡-

إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ
عِبَادٌ أَمۡثَالُكُمۡۖ فَٱدۡعُوهُمۡ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لَكُمۡ إِن
كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٩٤

"እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸው ብጤዎቻችሁ ባሮች (ተገዢዎች) ናቸው፤ እውነተኞችም እንደሆናችሁ ጥሩዋቸውና ለናንተ ይመልሱላችሁ ፤ (አይችሉም)።" (አል-አዕራፍ 7:194)

مَثَلُ ٱلَّذِينَ
ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوْلِيَآءَ كَمَثَلِ ٱلْعَنكَبُوتِ
ٱتَّخَذَتْ بَيْتًا ۖ وَإِنَّ أَوْهَنَ ٱلْبُيُوتِ لَبَيْتُ ٱلْعَنكَبُوتِ ۖ
لَوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ﴿٤١﴾

"የነዚያ ከአላህ ሌላ ረዳቶችን (ጣኦታትን) የያዙ ሰዎች ምሳሌ ቤትን እንደሰራች ሸረሪት ብጤ ነው ፤ ከቤቶችም ሁሉ በጣም ደካማው የሸረሪት ቤት ነው ፤ ቢያውቁ ኖሮ (አማልክት አድርገው አይገዟቸውም ነበር)።" (አል-ዐንከቡት 29:41)

ደግሞም በሁሉም ዘመንና ስፍራ ላሉት ባሮቹ አጠቃላይ የሆነ የአምልኮ (የዒባደ) መመሪያ ሲያስቀምጥ አላህ እንዲህ ይላል:-

أَلَا
لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلْخَالِصُ ۚ وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ
مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلْفَىٰٓ

"ንቁ! ፍጹም ጥሩ የሆነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው። እነዚያም ከርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች ያየዙት ወደ አላህ

ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንገዛቸውም (ይላሉ)፤ ... " (አል-ዙመር 39:3)

أَفَاتَّخَذْتُم مِّن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ لَا يَمْلِكُونَ لِأَنفُسِهِمْ نَفْعًا وَلَا ضَرًّا

"... ለነፍሶቻቸው ጥቅምንም ጉዳትንም የማይችሉን ረዳቶች ከርሱ ሌላ ያዛችሁን? በላቸው፤ ... " (አል-ረዕድ 13:16)

أَفَحَسِبَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ أَن يَتَّخِذُوا۟ عِبَادِى مِن دُونِىٓ
أَوْلِيَآءَ ۚ إِنَّآ أَعْتَدْنَا جَهَنَّمَ لِلْكَٰفِرِينَ نُزُلًا ١٠٢

"እነዚያ የካዱት ባሮቼን ከኔ ሌላ አማልክት አድርገው መያዛቸውን (የማያስቆጣኝ አድርገው) አሰቡን? እኛ ገሀነምን ለከሐዲዎች መስተንግዶ አዘጋጅተናል።" (አል-ከሕፍ 18:102)

أَمِ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ ۖ فَٱللَّهُ هُوَ ٱلْوَلِىُّ

"ከርሱ ሌላ ረዳቶችን ያዙን? (ረዳቶች አይደሉም)፤ አላህም ረዳት እርሱ ብቻ ነው።" (አል-ሹራ 32:9)

قُلْ أَغَيْرَ ٱللَّهِ أَتَّخِذُ وَلِيًّا فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ

"ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ከሆነው አላህ ሌላን አምላክ እይዛለሁኝ? በላቸው ፤ ... " (አል-አንዓም 6:14)

እነዚህ የቁርአን አናቅጽ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ልክ እንደዛሬዎቹ የሙታን አምላኪዎች ወደ አላህ ያቃርቡናል፣ ያማልዱናል በማለት ወሊዮችንና ሷሊሆችን ይጠሩ፤ ከነሱም ውስጥ አማልክት አድርገው በመያዝ በዱዓእ፣ በእርድ በነዝር፣

በጠዋፍ፣ በመፍራት (ኸውፍ) እና በመከጀል (ረጃእ) ሲገዟቸው የነበሩ መሆናቸው ያረጋግጣሉ። አልኩት።

## ሙሽሪኮች ያመልኳቸው የነበረው ጣዖታትን እራሳቸውን አይደለም።

እንደ ላት፣ ዑዛ፣ መናት የጉሥ፣ የዑቅና ነስር የመሳሰሉት ጣአታት የሚወክሉት እነዚያን ወሊዮችና ሷሊሆችን ነው፤ እነዚህ ስሞች የወሊዮቹና የሷሊሆቹ ስሞች ናቸው። ታዲያ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች ልክ እንደዛሬዎቹ ቁቡርዮች፣ ጣአታትን ሣይሆን የሚያመልኩት መልካም ሰዎች ናቸዉ ወይም ወሊዮችና ሷሊሆች ናቸው ብለዉ የሚጠረጥሩዎቻቸዉንና፣ በነሱ ስም እነዚህ ጣአታት የተሰየሙባቸዉን ሰዎች ናቸዉ።

በዚህም ሁለቱም (የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮችና የአሁኖቹ ቁቡርዮች) ወሊዮችን በማምለክ ረገድ አንድ መሆናቸው ግልጽ ይሆንልኃል። በሁለቱ መካከል ያለው ብቸኛ ልዩነት ሙሽሪኮቹ የአምልኮ ተግባራታቸውን የሚያከናውኑት የወሊዮቹን ስም በያዙት ሐውልቶች ዙሪያ፣ አስበውት የሚሄዱና የሚዞሩትም ወደ ሐውልቶቹ ሲሆን፤ የዛሬዎቹ ቁቡሪዮች ደግሞ በሐውልቶቹ ምትክ የወሊዮቹን ስም በያዙ ደሪሃዎችና በታዎች ዙሪያ ነው፤ የአምልኮ ተግባራቶቻቸውን የሚፈጽሙት፤ አስበውት የሚሄዱትና የሚዞሩበትም ወደ መቃብሮቹና በታዎቹ ነው። ታዲያ እውነተኛው አላማ

ወይም በእውነት የሚፈለጉት እነዚህ ሐውልቶች ወይም መቃብሮቹ የተሰየሙባቸው ሰዎች ናቸው።

አሁን ለምሣሌ አንድ የበደዊን መካነ መቃብር ዘየርኩ የሚለዉን ሰዉ ከየት ነዉ የምትመጣዉ ብለህ ብትጠይቀዉ ከሰይድ በደዊ ዘንድ ነዉ ይለሃል። እሱ የመጣው ከበደዊ ዘንድ አይደለም። በደዊን አላየዉም፣ አያዉቀዉምም ነገር ግን እሱ የሚመጣዉ በበደዊ ስም ከተሰየመዉ የመቃብር ስፍራ ወይም ታቦት ዘንድ ነዉ። የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮችም ይህንኑ ነዉ ሲያደርጉ የነበሩት። እነሱም በቀጥታ ወደ ላት ፣ የጉስና የዑቅ ሄደዉ ሣይሆን የነዚያን ወሊዮች ወይም ወሊይ ናቸዉ ብለዉ የገመቱዋቸዉን ሰዎች ስም ወደ ያዙት ሐውልቶችና ጣዖታት ነበር ይዞሩና ይሄዱ የነበሩት። አልኩት።

## ጣዖታት የቅዱሳን ሰዎች ስሞች እንጂ ሌላ አይደሉም

ጓደኛዬ እንዲህ አለኝ:- "የፊተኞቹ ሙሽሪኮች /ጣኦታዉያን/ ከድንጋይ፣ ከወርቅ ወይም ከነሐስ የተሰሩትን ጣኦታት፣ ሐውልቶችና ቅርፃ-ቅርጾ እራሳቸውን ላለማምለካቸዉና የሚያመልኩትም እነዚህ ሐውልቶችና ቅርፃቅርፆች በስሞቻቸዉ የተሰየሙትን ወሊዮችና ቅዱሳን ሰዎች ለመሆናቸዉ ምን ማስረጃ አለህ?"

እንዲህ አልኩት:- መገንዘብ የምትችል ብትሆን ኖሮ ይህ ነገር ግልጽ ማስረጃ ያለዉ ለመሆኑ ካለፉት የቁርአን አንቀጾች መረዳት በቻልክ ነበር ፤ ባሳለፍነዉ ዉይይታችን ዉስጥ የፊተኞቹ ሙሽሪኮች ወሊዮችንና ቅዱሳን ሰዎችን

እንጂ ሌላን እንደማያመልኩ በግልጽና በማያጠራጥር ሁኔታ የሚገልጹትን የቁርአን አንቀጾች አቅርቤልሃለሁ።
ይሁን እንጂ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግና ማሥረጃዉን ለማስፋት ያክል፣ እንዲሁም ጥርጣሬህን ሁሉ ለማስወገድ ስል ይህንን ንግግሬን የሚያጠናክርና አንተም በያዝከው አመለካከትህ እንድትገፋበት እያደረገህ ያለውን ጥርጣሬህን ሙሉ በሙሉ የሚያስወግድልህን ማስረጃ በአላህ ፈቃድ አወሳልሃለሁ።

## የጉሥ ፣ የዑቅና ነስር ከኑሕ ሕዝቦች ዉስጥ ቅዱሳን ሰዎች (ኋሊሆች) ነበሩ

1. ቡኻሪ የሚከተለዉን የኢብን ዐባስ ንግግር ዘግቦልናል፡- "በኑሕ ሕዝቦች ዉስጥ የነበሩ ጣዖታት ዐረብ ዉስጥ ሆኑ። በደዉመተል ጀንደል የሚገኘዉና "ወድ" የሚባለዉ ጣዖት የከልብ ጐሣ ጣዖት ነበር። "ሱዋዕ" የሁዘይል ጐሣ ጣዖት ነበር። "የጉሥ" ደግሞ የሙራድ ጐሣ ከዚያ በሰበእ (ሳበ) በሚገኘው ሐውፍ ወይም ጀርፍ በሚባል ቦታ የበኒ ገጢፍ ጣዖት ሆነ። "የዑቅ" የሀመዳን ጐሣ ጣዖት ነበር።"ነስር" የሒምየር ጐሣ የዚልከላዕ ዘሮች ጣዖት ነበር። ሁሉም ከኑሕ ሕዝቦች የሆኑ የቅዱሳን ሰዎች ስሞች ናቸዉ። እነሱ ሲሞቱ ሰይጣን መጣና ቅዱሳኑ ሰዎች ይቀመጡባቸዉ በነበሩት ቦታዎች ላይ ድንጋይ እንዲተክሉ (ሐዉልት እንዲሰሩ) እና ሐዉልቶቹንም በቅዱሳኑ ሰዎች ስሞች እንዲሰይሙዋቸዉ

ሰዎችን አነሳሳ። በሰይጣን ራዕይ መሠረት ሰዎች ይህንን አደረጉ። በዚያን ወቅት ሐዉልቶቹ አልተመለኩም ነበር። የኋላ ኋላ ግን የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ሲያልቁና እዉቀትም ሲጠፋ ተመለኩ። [1]

2. "አልአስናም" በተሰኘዉ መጽሐፉ ዉስጥ ገጽ 52 ላይ አልከልቢም ከኢብን ዐባስ ቃል ጋር የሚመሳሰል ቃል እንደሚከተለው አስፍሯል። " ከዚያም ሦስተኛዉ ክፍለ ዘመን ሲመጣ ከኛ በፊት የነበሩት ሰዎች እነዚህን ነገሮች (በቅዱሳኑ ሰዎች ስሞች የተሰሩትን ጣዖታት) ያከበሩትና ያላቁት በአላህ ዘንድ እንደሚያማልዷቸዉ ስለ ከጀሉ ነዉ እንጂ ለሌላ አይደለም በማለት ያመልኳቸዉ ጀመር።"

3. ወድ፣ ሱዋዕ፣ የጉሥ የዑቅና ነስር ስለሚባሉት ጣዖታት አስመልክቶ ሙሐመድ ቢን ካዕብ እንዲህ ብሏል፦ "እነዚህ በአደምና በኑሕ ዘመናት መካከል ያሉ የቅዱሳን ሰዎች ስሞች ናቸዉ። እነሱ ከሞቱ በኋላ የነሱን ፈለግ የሚከተሉና በአምልኮ ተግባራትም እነሱ የያዙትን ነገር የሚይዙ ተከታዮች ነበሩ። ኢብሊስ ወደነዚህ ተከታዮች በመምጣት ምስሎቻቸዉን ብትሰሩ ለዒባዳ የበለጠ ጉጉት ያሳድርባችኋል አላቸዉ። ኢብሊስ በነገራቸዉ መሠረት ምስሎቻቸዉን ሠሩ።

---

1. ከአላህ ሌላን የማምለክ ተግባር ነዉ በማለት አላህ(ሱ.ወ) በሙሽሪኮች ላይ የጠላቸዉ ነገሮች ዱዓ(ልመና)፣ ማረድ፣ ስለት(ነዝር) ፣ ፍራቻና ከጃሉት የመሳሰሉትን የአምልኮ ተግባራት ከአላህ ሌላ ላሉት በወሊዮችና በሷሊሆች ስሞች ለተሰየሙት ጣዖታት ማዋላቸዉ መሆኑ ካሳለፍነዉ ወይይታችን ግልጽ ይሆናል።

ከዚያም ከነሱ(እነዚህን ምስሎች ከሰሩት ሰዎች) በኋላ ሌላ ትዉልድ መጣ። ከዚያም ኢብሊስ ወደ አዲሱ ትዉልድም መጣና "ከናንተ በፊት የነበሩት ሰዎች እነዚህን ምስሎች ይገዟቸዉ ነበር" አላቸዉ። ከዚያም ይገዟቸዉ ጀመር።

*የጣዖት አምልኮት የተጀመረው መች ነው?*

የጣዖት አምልኮት የተጀመረው ከዚያ ነበር ፣ እነዚያ ጣዖታት በነዚያ ቅዱሳን ሰዎች ምስል ስለተሰሩ በነሱም ስሞች ተሰየሙ። ኢብኑ ጀሪር ይህን ሙሐመድ ቢን ቀይስ የተናገረውን እንደሚከተለው ዘግቧል:-

"እነሱ በአደምና በኑሕ ዘመን መሀከል የነበሩ ቅዱሳን ሰዎች (ሷሊሒን) ነበሩ ፣ በነሱ የሚመሩ ተከታዮች ነበሯቸው፤ እነዚህ ተከታዮች "በምስል ብናስቀምጣቸው ይበልጥ እንድንገዛቸው ያነሳሳነል" ብሎ ሳሉዋቸው።

ይህንን አቋም ዒክሪማ ፣ አልደሓክ ፣ ቀታዳና ኢብኑ ኢስሓቅም ደግፈወታል።

*አል-ላት ለሐጃጆች በሶ የሚሰራ ሰዉ ነበር*

4. አል-ላት ተብሎ ስለሚታወቀዉ ጣዖት ቡኻሪ ከኢብኑ ዐባስ የሚከተለዉን ዘግቧል:- "አል-ላት ለሐጃጆች በሶ የሚሰራ ሰዉ ነበር።" ኢብኑ አልከልቢ "አልአስናም" በተሰኘዉ መጽሐፉ ዉስጥ በገጽ 16 እንዲህ ብሏል:- "አል-ላት በጧኢፍ

ይገኝ ነበር፣ (መመለክ የተጀመረዉም) ከመናት በኋላ ነበር። ባለአራት ማእዘን ቋጥኝ ነዉ፣ አንድ አይሁዳዊ በሱ አጠገብ በሶ ይሰራ ነበር። ይህም ከኢብን ዐባስ ንግግር ጋር ይመሳሰላል: (አል-ላት ማለት በሶ አበስባሽ ማለት ነዉ)

5. "አልሚለል ወንኒሐል" በተሰኘዉ መጽሐፉ ዉስጥ አሽሽሀረስታኒ እንዲህ ይላል:-

ጣዖታት የሚደረጉት በቦታዉ የሌለ ግን ይመለክ የነበረ ሰዉ ነበረበት ተብሎ በሚገመት በታ ላይ ነዉ፣ ከዚያም በሱ ምስልና ቅርፅ የተሰራዉ ጣዖት በሱ ምትክ ይመለካል፣ ይህ ካልሆነማ አንድ አዕምሮ ያለዉ ሰዉ እንጨት ጠርቦ ምስል በመሥራት አምላክ ነዉ ብለዉ እንደማያምን በትክክል እናዉቃለን።" ነገር ግን ሰዎች ያለ አላህ ፈቃድ ያለማስረጃና ማረጋገጫ ወደነዚህ ጣዖታት (በዒባዳ) ፊታቸዉን ማዞር ሲያዘወትሩ፣ ጉዳዮቻቸዉንም ከጣዖቶቹ ጋር ሲያስተሳስሩ (እነሱ ይፈጽሙልናል ሲሉ) ይህ ድርጊታቸዉ ዒባዳ ሆነ። ጉዳዮቻቸዉን እንዲፈጽሙላቸዉ ከነሱ(ከጣዖቶቹ) መጠየቃቸዉ ደግሞ አምላክነትን ለነሱ ማረጋገጥ ነዉ። ስለዚህም ድርጊታቸዉ እንዲህ ይሉ ነበር:-

مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلْفَىٰٓ

"…. ወደ አላህ እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አናመልካቸዉም…"

(አል-ዙመር 39:3)

ከዚህ በኋላ (ይህ ሁሉ ማስረጃ ከተነገረህ በኋላ) ጣዖታት የተሰሩት በነዚያ ሕዝቦቻቸዉ መልካም ሰዎች መሆናቸዉን ባመኑባቸዉና በወደዷቸዉ ሰዎች ስም መሆኑንና የሚመለኩትም እነሱ ራሳቸዉ ሳይሆኑ ለነዚያ በስሞቻቸዉ ለተሰሩት ሰዎች ሲባል መሆኑን ቅንጣት ታክል ትጠራጠራለህን? አልኩት።

<u>በመጽሐፉ አዘጋጅ የተፈታዉ የቀብር አምላኪ ትልቁ ችግር</u>

ጓደኛዬ እኔ እስካሁን ባቀረብኩለት ማብራሪያ ምክንያት እጅ የመስጠት ምልክት እየታየበት "ግን ነገሩ አሁንም ብዙ ችግሮች አሉበት።" አለ።

እኔም፡- ያስቸገረህን ነገር ግለጽልኝ ፤ በአላህ ፈቃድ በዚህ ነጥብ ላይ ያስቸገረህን ሁሉ አብራራልሃለሁ። አልኩት። እሱም "እስከ አሁን ባመጣሃቸው የቁርአን አንቀጾችና የቀደምት ምሁራን ንግግሮች የፈተኞቹ ሙሽሪኮች ወሊዮችንና ሷሊሆችን እንጂ ሌላን እንደማያመልኩ ለማረጋገጥ እንደምትፈልግ ግልጽ ነዉ፣ በዚህ ደግሞ አንተ እንደምትላቸዉ "ቁቡሪዮን" (ቀብር አምላኪዎች) ወሊዮችንና ሷሊሆችን እንደሚያመልኩ በ"ቂያስ" ለማረጋገጥ ፈልገህ እንደሆነ ግልጽ ነው።"

"ነገር ግን ካቀረብካቸዉ አንቀጾች ዉስጥ የቀድሞዎቹ ሙሽሪኮች በእዉነት የሚያመልኩት ጣዖታትን ራሳቸዉን መሆኑን የሚገልጹ አንቀጾች አሉ። በእዉነት የሚያመልኩት ጣዖታትን ሳይሆን በስሞቻቸዉ የተሰየሙባቸዉን ወሊዮችና ሷሊሆች ቢሆን ኖሮ አላህ ይህን እዉነታ በገለፀልን ነበር።

እነዚያን ወሊዮች እንጂ ሌላን የማይገዙና ጣዖታትም በአላህ ዘንድ እንደሚያማልዷቸዉ ባይተማመኑባቸዉ ኖሮ ቁርአንም ሙሽሪኮችን ሲወቅስ ወቀሳዉ ወሊዮችን በመገዛታቸዉ ብቻ ላይ የተወሰነ በሆነ ነበር።"

"ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ቁርአን ዉስጥ ለሙሽሪኮች የተደረጉት አብዛኞቹ ማስጠንቀቂያዎችና ወቀሳዎች የተመረኮዙት ሙሽሪኮች ጣዖታትን እንዳያመልኩ የሚል ነዉ።:- አስናም፣ አዉሳን፣ አንሳብ እንዳያመልኩ የሚል ነዉ።

فَٱجْتَنِبُوا۟ ٱلرِّجْسَ مِنَ ٱلْأَوْثَٰنِ وَٱجْتَنِبُوا۟ قَوْلَ ٱلزُّورِ ﴿٣٠﴾

"... ከጣዖታትም ርክሰት ተጠንቀቁ፣ ሐሰትንም ቃል ራቁ።" (አል-ሐጅ 22:30)

إِنَّمَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوْثَٰنًا وَتَخْلُقُونَ إِفْكًا

" ከአላህ ሌላ የምታመልኩት ጣዖታትን ብቻ ነዉ፣ ዉሸትንም ትቀጣጥፋላችሁ፣..." (አል-ዐንከቡት 29:17)

وَقَالَ إِنَّمَا ٱتَّخَذْتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ أَوْثَٰنًا مَّوَدَّةَ بَيْنِكُمْ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا

" (ኢብራሂም) አለም:- ከአላህ ሌላ ጣዖታትን (አማልክት አድርጋችሁ) የያዛችሁት በቅርቢቱ (በዓለማዊ) ሕይወት በመካከላችሁ ለመዋደድ ብቻ ነዉ፣..."

(አል-ዐንከቡት 29:25)

فَأَتَوۡاْ عَلَىٰ قَوۡمٖ يَعۡكُفُونَ عَلَىٰٓ أَصۡنَامٖ لَّهُمۡۚ

"..... የራሳቸዉን ጣዖታት በማምለክ ላይ በሚዘወትሩ ሕዝቦች ላይ አለፉም፣...." (አል-አዕራፍ 7:138)

وَإِذۡ

قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ رَبِّ ٱجۡعَلۡ هَٰذَا ٱلۡبَلَدَ ءَامِنٗا وَٱجۡنُبۡنِي وَبَنِيَّ أَن نَّعۡبُدَ ٱلۡأَصۡنَامَ ٣٥

" (ኢብራሂምም ባለ ጊዜ አስታዉስ)፡- ጌታዬ ሆይ! ይህንን አገር (መካን) ፀጥተኛ አድርገዉ፣ እኔንም ልጆቼንም ጣዖታትን ከመገዛት አርቀን፣" (ኢብራሂም 14:35)

۞ وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ ءَازَرَ أَتَتَّخِذُ أَصۡنَامًا ءَالِهَةً

" ኢብራሂምም ለአባቱ አዘር ጣዖታትን አማልክት አድርገህ ትይዛለህን? . . . ባለ ጊዜ(አስታወስ) " (አል-አንዓም 6:74)

قَالُواْ نَعۡبُدُ أَصۡنَامٗا فَنَظَلُّ لَهَا عَٰكِفِينَ ٧١

"ጣዖታትን እናመልካለን፣ እርሷንም በማምለክ ላይ እንቆያለን፣ አሉ።" (አል-ሹዐራ 26:71)

وَتَٱللَّهِ لَأَكِيدَنَّ أَصۡنَٰمَكُم بَعۡدَ أَن تُوَلُّواْ مُدۡبِرِينَ ٥٧

"በአላህም እምላለሁ፣ ወደ ኋላ ዞራችሁ ከሄዳችሁ በኋላ ጣዖቶቻችሁን ተንኮል እሰራባቸዋለሁ(አለ)።" (አል-አንቢያ 21: 57

﴿ وَلَقَدْ ءَاتَيْنَآ إِبْرَٰهِيمَ رُشْدَهُۥ مِن قَبْلُ وَكُنَّا بِهِۦ عَٰلِمِينَ ﴿٥١﴾ إِذْ قَالَ لِأَبِيهِ وَقَوْمِهِۦ مَا هَٰذِهِ ٱلتَّمَاثِيلُ ٱلَّتِىٓ أَنتُمْ لَهَا عَٰكِفُونَ ﴿٥٢﴾

"ለኢብራሂምም ከዚያ በፊት ቅን መንገዱን በእርግጥ ሰጠነው፤ እኛም በርሱ (ተገቢነት) አዋቂዎች ነበርን። ለአባቱና ለሕዝቦቹ ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ ያቺ እናንተ ለርሷ ተገዢዎች የሆናችሁት ምንድንናት? ባለ ጊዜ (መራነው)።" (አል-አንቢያ 21፡51-52)

"እነዚህ የቁርአን አናቅጽ ሙሽሪኮች ይገዟቸዉ የነበሩት ጣዖታትን ራሳቸዉን ለመሆኑ በግልጽ ያስረዳሉ። ስለዚህም ነዉ ወሊዮችን ማምለክ እንደተከለከለ ሁሉ ጣዖታትንም ማምለክ በግልጽ የተከለከለው።" አለ።

## *ጣዖታትን ማምለክ ወሊዮችን ማምለክ ነዉ*

እንዲህ አልኩት፡- አዎን! ጣዖታትንና ወሊዮችንም ማምለክ በርግጥ ተከልክሏል። ይህ ደግሞ በቁቡሪዮች ላይ ከአላህ ሌላ የማምለክ ፍርድ ያሰጠል ፤ ምክንያቱም ወሊዮችን እያመለኩ ነውና። በቁርአን ዉስጥ ከአላህ ሌላን ማምለክ የከለከለበት ጣዖታትን አጣምሮ በማዉሳት ወሊዮችን ሳይጠቅስ ያለፈ ቢሆን እንኳ ቁቡሪዮችን ከወሊይ አምላኪዎች እንቆጥራለን፣ ምክኒያቱም እነዚያ ወሊዮች ከአላህ ሌላ (አማልክት) ናቸዉና። ሙሽሪኮች ለጣዖቶቻቸዉ የሚፈጽሙትን የአምልኮ ተግባራት ማለትም ዱዓ፣ ማረድ፣ ስለት፣ ፍራቻ፣ ክጃሎት የመሳሰሉትን ተግባራት ቁቡሪዮችም ለነዚያ ወሊዮች

ነገር ግን ከአሁን በፊት በግልጽ ማስረጃዎች እንዳብራራሁልህ እርግጠኛዉ ነገር ሙሽሪኮች የሚያመልኩት ወሊዮችንና ኗሊሆችን ራሳቸዉን መሆኑ ነዉ። ጣዖታትንና ቅርጻቅርጾችን የሚያመልኳቸው በእዉነት የሚያመልኳቸዉን ወሊዮችና ኗሊሆች በመወከልና በነሱ ስሞች ጣዖታትን በመሥራት ነዉ እንጂ በእዉነት የሚገዙት ጣዖታትን አይደለም።

ስለዚህም አላህ (ሱ.ወ) አንዳንዴ ጣዖት አምላኮዎች ይላቸዋል። አንዳንዴ ደግሞ የወሊይ አምላኮዎች ይላቸዋል። ወደ ጣዖቶቹ በመሄድ እነሱን በመዞራቸዉ (ጠዋፍ በማድረጋቸዉ)፣ በነሱ ዙሪያ ተቀምጠዉ እነሱን በማምለካቸውና ቁርባኖችን ለነሱ በማቅረባቸዉ ምክንያት የጣዖት አምላኪዎች ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የነዚህን ጣዖታት ባለቤቶች ስለሚጣሩ፣ ጉዳዮቻቸዉን እንዲፈጽሙላቸዉ ስለሚጠይቋቸዉና አላህ ሳይፈቅድላቸዉ አለህ ዘንድ ያማልዱናል ብለዉ ስለሚመኩባቸው የወሊይ አምላኪዎች ናቸዉ እንላለን።

የአሁኑ ዘመን ቀብር አምላኪዎችም እንዲሁ ናቸዉ። የቀብር መጋረጃዎችን ይስማሉ፣ በቀብር ዙሪያ ጠዋፍ ያደርጋሉ፣ መቃብሮችን ያሳምራሉ፣ ቁባዎችን ይገነቡባቸዋል፣ ስለት ያቀርቡላቸዋል፣ ስለዚህም እነሱ በግልጽ የመቃብር

አምላኪዎች ሲሆኑ ዉስጥ ዉስጡን ግን የወሊዮች አምላኪዎች ናቸዉ።

ነገር ግን መቃብሩን በሚዞሩበት ጊዜ (በነዋፍ በሚያደርጉበት ጊዜ) የመቃብሩን ባለቤት ሟች ይጠራሉ፣ እንዲረዳቸዉም ይጥይቃሉ፣ ከነሱም በረከትን ይፈልጋሉ። በዚህ መልኩ ስናይ ግን በግልጽ የሚያመልኩት ወሊዮችን ሲሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያመልኩት መቃብሩን ነዉ።

ስለዚህ ለመቃብሮች የሚያደርጉትን ተግባር በማየት የቀብር አምላኪዎች ብለህ ብትጠራቸዉም ትክክል ነህ። በሌላ በኩል ደግሞ "ዱዓ" (ልመና) ፣ ነዝር (ስለት)፣ መሐላ፣ ፍራቻና ከጀሎት በመሳሰሉት የአምልኮ ተግባራት ወሊዮችን ስለሚያመልኩ የወሊይ አምላኪዎች ብለህ ብትጠራቸዉም ትክክል ነህ። በሁለቱም መልኩ ሲታዩ ትልቁን ሽርክ መፈፀማቸዉ ግልፅ ነዉ። የስሜት ተገዢዎች (አምላኪዎች) ብትላቸዉም ትክክል ነህ።

የቀብር አምላኪ የተሞከረዉ በስሜቱ ናዉና ። ስሜቱ እንዲጠም አደረገዉ፣ ስሜቱንም አመለከ። የቀብር አምላኪ በሚያመልከዉ ቀብር ዉስጥ ምስል የሚሰራዉና ቀብሩንም የሚያሳምረዉ በስሜቱ በመገፋፋት ነዉ።

"ደዕወቱል ሐቅ" በተሰኘዉ መጽሐፋቸው ገጽ 62 ላይ ኡስታዝ ዐብዱራህማን አልወኪል ያሉትን ስማ፦

**_مَن "መን" እና ما "ማ" የሙሽሪኮችን አማልክት ይወክላሉ_**[1]

ቁርአን አንዳንዴ አንድን የተወሰነ ነገር ለመግለጽ በአንድ ቦታ ላይ "መን" ን ተጠቅሞ በሌላ ቦታ ደግሞ ያንኑ ነገር መልሶ ለመግለጽ "ማ"ን መጠቀሙ የራሱ የአገላለጽ ዘይቤ ነዉ። በአንድ ቦታ ላይ ሕሊና ያለዉን (ሰውን) የሚያመለክት ቃልም ሆነ ሕሊና የሌለውን ነገር (ከሰዉ ዉጭ ያለን ነገር) የሚያመለክት ቃል ይጠቀማል። በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለቱንም ቃላት እየለዋወጠ (አንዱን በሌላኛዉ ቦታ እየተካ) ይጠቀማል።

በ "ማ" ለመግለጽ የተፈለገዉ ሕሊና የሌለውን ነገር (ከሰዉ ዉጭ የሆነን ነገር) ከሆነ የተፈለገዉ በወሊዮቹ ስሞች የተሰሩት ጣዖታትና ቅርጻቅርጾች ነዉ ማለት ነዉ። በሁለቱም አገላለጾች የተገለፁት ነገሮች አንዱ ከሌላዉ አይለይም። ምክንያቱም ሁለቱም ያ ከአላህ ሌላ የሚመለከዉን ነገር ስለሚወክሉ ነዉ።
"መን" የሚመለከዉን ነገር (ወሊይ ወዘተ...) ራሱን ይወክላል። "ማ" ደግሞ በተመላኪዉ ወሊይ ስም የተሰራዉን ጣዖት ወይም ቀብር ይወክላል።

---

1. "መን" የሚለዉ የዐረብኛ ቃል በዚህ አገባቡ "እሱ" ማለት ነው። "ማ" የሚለውም "እሱ" ማለት ነው። "መን" የሚለዉን ቃል የምንጠቀመዉ ለሰዉ ነዉ። "ማ" የሚለዉን ቃል ግን የምንጠቀመዉ ከሰዉ ዉጭ ላለ ነገር (ሕሊና ለሌለው ነገር) ነዉ። ተርጓሚዉ

وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن

لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَـٰمَةِ

"ወመን አደልሉ ሚመን የድዑ ሚን ዱኒልላሂ "መን" ላ የስተጂቡ ለሁ ኢላ የዉሚልቂያማ"

" እስከ ተንሳኤ ቀን ድረስም ለርሱ የማይመልስለትን (ጣዖት) ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰዉ ይበልጥ የተሳሳተ ማን ነዉ?..

(አል-አሕቃፍ 36:5)

በዚሁ ምዕራፍ ዉስጥ ከላይ ከተጠቀሰዉ አንቀጽ በፊት የሚከተለዉ ሰፍሯል:-

قُلْ أَرَءَيْتُم مَّا تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَرُونِى مَاذَا خَلَقُوا۟ مِنَ ٱلْأَرْضِ

"ቁል አረ አረአይቱም "ማ" ተድዑነ ሚንዱኒልላሂ አሩኒ ማዛ ኸለቁ ሚነል አርድ..."

"ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸውን አያችሁን? ከምድር ምንን እንደፈጠሩ አሳዩኝ ፤ . . . በላቸው።"

(አልአሕቃፍ 36: 4)

አንድን ነገር በ"መን" ም በ"ማ"ም ገለጸ ማለት ነዉ።

ስለዚህም የቀብር አምላኪዎች በሚያመጡት ማምታቻና ሐሰተኛ ሐሳብ አትታለል። ለጃሂሊያዉ ሽርክ ይጠሯቸው የነበሩት ጣዖታት ናቸዉ፣ ስለዚህም አላህ ጣዖታትን ለመግለጽ "ማ"ን ተጠቀመ። "ማ" ደግሞ የሚያገለግለዉ ከሰዉ ዉጭ ላለ ነገር ነዉ።

እኛ ግን "የምንጠራው ወሊዮችን ነው።" በማለት ለማምታታት ይሞክራሉ።

አንተ ግን ቀደም ብዬ እንዳብራራሁልህ የ"መን" ንና የ"ማ"ን አጠቃቀም አውቀሃል፣ በአንድ ነገር ላይ ሁለቱንም መጠቀም እንደሚቻልና ሁለቱም ሊተካኩ እንደሚችሉ አይተሃል።

وَٱتۡلُ عَلَيۡهِمۡ ﴿٦٨﴾
نَبَأَ إِبۡرَٰهِيمَ ﴿٦٩﴾ إِذۡ قَالَ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦ مَا تَعۡبُدُونَ ﴿٧٠﴾ قَالُواْ
نَعۡبُدُ أَصۡنَامًا فَنَظَلُّ لَهَا عَٰكِفِينَ ﴿٧١﴾ قَالَ هَلۡ يَسۡمَعُونَكُمۡ إِذۡ
تَدۡعُونَ ﴿٧٢﴾ أَوۡ يَنفَعُونَكُمۡ أَوۡ يَضُرُّونَ ﴿٧٣﴾ قَالُواْ بَلۡ وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا
كَذَٰلِكَ يَفۡعَلُونَ ﴿٧٤﴾ قَالَ أَفَرَءَيۡتُم مَّا كُنتُمۡ تَعۡبُدُونَ ﴿٧٥﴾ أَنتُمۡ
وَءَابَآؤُكُمُ ٱلۡأَقۡدَمُونَ ﴿٧٦﴾ فَإِنَّهُمۡ عَدُوٌّ لِّيٓ إِلَّا رَبَّ ٱلۡعَٰلَمِينَ

" በነሱም (በሕዝቦችህ) ላይ የኢብራሂምን ወሬ አንብብላቸው። ለአባቱና ለሕዝቦቹ ምንን ታመልካላችሁ ባለ ጊዜ፣ ጣዖታትን እናመልካለን። እነርሱንም በማምለክ ላይ እንቆያለን ፣ አሉ። (እርሱም) አለ፦ በጠራችኋቸው ጊዜ ይሰሟችኋልን? ወይስ ይጠቅሟችኋልን? ወይስ ይጎዷችኋልን? የለም አባቶቻችን እንደዚሁ ሲሰሩ አገኘን አሉት። ታመልኩት የነበራችሁትን አስተዋላችሁን? እናንተም የቀድሞዎቹ አባቶቻችሁም

(ያመለካችሁትን)፣ እነሱም (ጣዖቶቹ) ለኔ ጠላቶች ናቸዉ፤ ግን የዓለማት ጌታ ሲቀር (እርሱ ወዳጄ ነዉ)።

(አልሹዐራእ 26፡ 69-77)

ሙሽሪኮቹ "ጣዖታትን እናመልካለን፣ እነርሱንም በማምለክ ላይ እንቆያለን።" ካሉ በኋላ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ( هل يسمعونكم ) "... ሀል የስመዑነኩም"

"..... ይሰሟችኃልን?" አሉ።

"ሀል የስመዑነኩም? " ያሉበት ምክንያት እሳቸዉ ለማለት የፈለጉት ጣዖታቱ በስሞቻቸዉ የተሰሩላቸዉን ሰዎች እንደሆነ እድታወቅ ነዉ።

ያለዚያ "ሀል ተስማዑኩም?" ማለት ነበረባቸዉ።[1] ከዚያም "ታመልኩት የነበራችሁትን አስተዋላችሁን?" አሉ። ቀጥለዉ "ፈእንነሁም ዐዱዉን ሊ ኢልላረበል ዓለሚን" "እነሱም ለኔ ጠላቶች ናቸዉ፣ ግን የዓለማት ጌታ ሲቀር" አሉ ። እዚሀ ላይ ኢብራሂም በዚሀ ንግግራቸዉ ለማለት የፈለጉት ጣዖታትንና በስሞቻቸዉ የተሰሩላቸዉን ሰዎች ነዉ። ያለዚያ "ፈ እንነሁም" ሳይሆን "ፈእንነሃ" ማለት ነበረባቸዉ። "ፈእንነሁም" የሚባለዉ ለሰዉ ነዉ። "ፈእንነሃ" የሚባለዉ ግን ሰዉ ላልሆነ ነገር ነዉ።

---

1. "ሀል የሰመዑነኩም?" የሚለዉ ለሰዎች ይሰሟችኋልን? ማለት ሲሆን "ሀል ተስማዓኩም" ማለት ደግሞ ከሰዎች ዉጭ ላለ ነገር ይሰሟችኃልን? ወይም ትሰማችኋለችን? ማለት ነዉ። ለሰዉም (ለሴት) "ሀል ተስማዑኩም?" ትሰማችኋለችን? ይባላል። ተርጓሚዉ

በአንድ ዘገባ ዉስጥ የሙሽሪኮችን አማልክት የሚያወሱ ሌሎች የቁርአን አናቅጽ በዚሁ መልኩ ይታያሉ። ቃላቶቹ ሰዎችን ወይም ከሰዉ ዉጭ ያሉትን ነገር ለመግለጽ ይሆናሉ። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም እንደተብራራዉ አንድ ሙሽሪክ አንድን ወሊይ ሲያመልክ ወሊዩን በማስከተል ብዙ አማልክቶችን ያመልካል። ለምሳሌ በወሊዩ ስም የሰራዉን ጣዖት ወይም ቀብር ወይም መጋረጃ ያመልካል።

አላህ እነሱን የአማልክት፣ የጣዖታትና የቅርጻ-ቅርጽ አምላኪዎች ወይም አጋሪዎች ያለበትን ምክንያት አብራርቼልሃለሁ። ይኅ ሁሉ አምልኮት የመነጨዉ ከወሊይ አምልኮት መሆኑንና በኋሊሆች መፈተን ለሽርክ ምክንያት እንደሚሆን ከማብራሪያዉ ለማመን ትችላለህ።

ሙሽሪኮች ስለሚያመልኩት ነገር ስያሜ ልዩነት ካየህ ልዩነቱ ከትርጓሜ ብቻ ነዉ። የሚሰየመው ነገር አንድ ነዉ። ከነዚህ ከአላህ ሌላ ለሚመለኩ ነገሮች ስያሜ መለያየት ምክንያት የሆኑትን ትርጓሜዎች ኡስታዝ ዐብዱራህማን አልወኪል "ደዕወቱልሐቅ" በተሰኘዉ መጽሐፋቸዉ ዉስጥ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

"እነሱ የሚያመልኩት "ወሊይ" ተብሎ የሚሰየመዉ ወይም የሚገለፀዉ በዱዓና በመሳሰሉት ወደሱ ስለሚቃረቡ ፣ ስለሚከተሉትና ስለሚወዱት (ሙዋላ ስለሚያደርጉ) ነዉ። ይህ መሠረታዊ ስያሜ ወይም አገላለጽ ነዉ። "ሸሪክ" ተብሎም ይገለጻል። ይህ ደግሞ በአምልኮታቸዉ ከአላህ ጋር

ስለሚያጋሩት ነዉ። "ኢላህ" (አምላክ)ም ይባላል። ምክንያቱም ያን የሚያመልኩትን ነገር በአምልኮት፣ ወደሱ በመጠጋት፣ ከሱ እርዳታን በመለመንና በመሳሰሉት ተግባራት ሙሉ በሙሉ የአምላክን ባህሪ ስለሰጡት ነዉ። "ወሠን"፣ "ሰነም" ወይም "ትምሳል" ም ይባላል። ይህ ደግሞ በዚያ ተሰርቶ በሚታየው ወይም በሚዳሰሰው ነገር በራሱ ወይም በተመሳኪዉ ወሊይ ስም በሚሰራዉ ነገር ሲገለጽ ነዉ። "ጣጉት" ተብሎም ይገለፃል፣ ይህ ደግሞ ስላጠመማቸዉና በሱ ምክንያት ስለጠመሙ ነዉ። "ሸይጣን"ም ይባላል፣ ምክንያቱም እነዚህን አማልክቶች እንዲያመልኩ በዋናነት የሚያነሳሳዉ ሸይጣን ስለሆነ ነዉ።

إِن يَدْعُونَ مِن دُونِهِۦٓ إِلَّآ إِنَٰثًا وَإِن يَدْعُونَ
إِلَّا شَيْطَٰنًا مَّرِيدًا ﴿١١٧﴾

"ከርሱ (ከአላህ) ሌላ እንስታትን እንጂ ሌላን አያመልኩም፣ አመጠኛ ሰይጣንንም እንጂ ሌላን አያመልኩም።"

(አል-ኒሳእ 4:117)

በአንድ አንቀጽ ዉስጥ እንስትም ሰይጣንም በማለት የሚመለከዉን ነገር ገለጸ። ነቢዩላህ ኢብራሂምም ለአባታቸዉ እንዲህ አሉ፡-

يَٰٓأَبَتِ لَا تَعْبُدِ ٱلشَّيْطَٰنَ

"አባቴ ሆይ! ሰይጣንን አታምልክ፣. . . " (መርየም 19:44) የሚመለከዉ ነገር " ጥርጣሬ" ወይም "ግምት" (ዟን) ተብሎም ይገለፃል። ምክንያቱም የሚያመልኩት ነገር ጥቅምም ሆነ ጉዳት ያመጣል ብለዉ ስለሚገምቱ ነዉ። "ዝንባሌ" (ሐዋ)ም ይባላል። ምክንያቱም ሙሽሪኮች የዝንባሌያቸዉ ተገዢ ስለሆኑ ነዉ።

وَمَا يَتَّبِعُ ٱلَّذِينَ
يَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ شُرَكَآءَ ۚ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا
ٱلظَّنَّ وَإِنْ هُمْ إِلَّا يَخْرُصُونَ ٦٦

"…. እነዚያ ከአላህ ሌላ ተጋሪዎችን የሚጠሩ ምንን ይከተላሉ? ጥርጣሬን እንጂ ሌላ አይከተሉም፣ እነሱም የሚዋሹ እንጂ አይደሉም። " (ዩኑስ 10:66)

إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَمَا تَهْوَى ٱلْأَنفُسُ ۖ
وَلَقَدْ جَآءَهُم مِّن رَّبِّهِمُ ٱلْهُدَىٰٓ ٢٣

"…… ከጌታቸዉም መመሪያ የመጣላቸዉ ሲሆኑ ጥርጣሬንና ነፍሶች የሚዘነበሉትን እንጂ ሌላ አይከተሉም።" (አል-ነጅም 53:23)

أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَـٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ

" ዝንባሌዉን አምላኩ አድርጎ የያዘዉን አላህም ከእዉቀት ጋር ያጠመመዉን .....አየህን?" (አል-ጃሢያ 35:23)

የሚያመልኩዋቸው ነገሮች ተሰያሚዎቹ በእውን የሌሉ (ስሞች) "አስማእ" ተብሎም ይጠራሉ። ይህ ደግሞ እውነታው ታይቶ ነው። እዉነተኛ ወሊይ አላህ ሆኖ ሳለ ተመላኪዎቻቸዉን "ወሊዮች" ብለዉ ስለሰየሚቻቸዉ ነዉ። (አማላጆች) "ሹፈዓእ" ተብሎም ይጠራሉ። የምልጃ ፈቃድ በእጁ ያለዉ አላህ ብቻ ነዉ።

﴿٣٩﴾ مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِۦٓ إِلَّآ أَسْمَآءً سَمَّيْتُمُوهَآ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُم مَّآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا مِن سُلْطَٰنٍ

"ከርሱ (ከአላህ) ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸዉን ስሞች እንጅ ሌላ አታመልኩም አላህ ስለነርሱ (ስለ ስሞቹ) ምንም ማስረጃ አላወረደም፣.....)

(ዩሱፍ 12፡ 40)

ሙሽሪኮች ለተመላኪዎቹ የተለያዩ መገለጫዎችን መስጠታቸዉ አያታልህ። የተለያየ መገለጫ ቢሰጠዉም ከአላህ ሌላ የሚመለከዉ ነገር ሁሉ አምልኮት ተገቢ አይሆንለትምና። የቅድመ ኢስላም ጃሂሊያ ሙሽሪኮች በአላህ ያጋሩት ጣዖታትን በማምለክና አማልክት ናቸዉ ብለዉ በመሰየም ነዉ፣ እነዚህ ግን የሚጠሩት (የሚያመልኩት)

ወሊዮችን ነዉ የሚለዉ አባባል ተቀባይነት የለዉም።
በቁርአን ዉስጥ እዉነቱ በትክክል ተብራርቷልና።

بسم الله الرحمن الرحيم

الحمد لله وحده والصلاة والسلام على من لا نبي بعده وعلى آله وصحبه ومن اقتدى بهداه إلى يوم الدين .

وبعد/ فيسر جمعية الدعوة والثقافة الإسلامية بأديس أبابا أن تقدم للقراء الكرام ترجمة كتاب "كيف نفهم التوحيد" للشيخ محمد أحمد باشميل لكي يفهموا حقيقة التوحيد والشرك ؛ والكتاب يعرض التوحيد الذي هو أساس الدين الإسلامي الذي لا يسع كل مسلم أن يستغني عنه بأسلوب سهل وميسر باالإعتماد على الكتاب والسنة الصحيحة ، على أسلوب المناقشة الذي جرت بين المؤلف وصاحبه الذي كان لا يختلف معه إلا في موضوع واحد فقط وذلك هو التوحيد ومايضاده (الشرك) .

وقد بذلت الجمعية كل جهدها في إخراج هذه الترجمة على الوجه المطلوب ، وبما أن عمل البشر لا يخلو من خطاء فإن الجمعية ترجو من القراء الكرام أن يزودوها بلمحوظاتهم واقتراحاتهم البناءة للاستفادة منها في الطباعة القادمة إن شاء الله تعالى.

هذا ، وتشكر الجمعية كل من يتعاون معها في تطوير ترجمة ونشر الكتبَ الإسلامية باللغات المحلية وذلك لنشر الإسلام بين الشعوب الإثيوبية.

ونسأل الله تعالى أن يوفق الجميع لما يحبه ويرضاه .

جمعية الدعوة والثقافة الإسلامية

أديس أبابا - إثيوبيا

١٤٢١/١٢/٨٢ هـ

١

# كيف نفهم التوحيد

تـــألـــيف

**محمد أحمد باشميل**